**ደራሲው ከአሁን በፊት ያሳተማቸው**

1. ኅብረ ብዕር 1ኛ መጽሐፍ
2. ኅብረ ብዕር (የብዕር ዘመራ) ሁለተኛ መጽሐፍ
3. ምንኵስና በኢትዮጵያ ዛሬና ትናንትና
4. የአሁኑ ‹‹ብፁዓን እነማን ናቸው?››

**ለኅትመት የተዘጋጁ መጻሕፍት**

1. ባህልና ክርስቲያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ
2. የምናምንቴዎች ዘመን
3. ሀገር በቀል ዕፅዋት

❖ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ባህልና አየር ንብረት ለውጥ አንጻር

ዋጋ ብር 20.00
US. D 10.00

# ብፁዓን እነማን ናቸው?



## ካሕሳይ ገብረእግዚአብሔር

2ኛ እትም

# ብፁዓን እነማን ናቸው?

አዲስ አበባ ሐምሌ 2004 ዓ.ም

መታሰቢያነቱ፡- ለታላቁ አባት ለአቡነ አበከረዙን ይሁንልኝ፡፡

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Right Reserved

# ማውጫ


መቅድም ........ 3
ብፁዓን እነማን ናቸው? ........ 5
የብፁዓን ተምሳሌቶች ........ 8
ሐዋርያትና ብፅዕና ........ 12
ኢትዮጵያውያንና ብፅዕና ........ 15
ብፅዕናና ጵጵስና በኢትዮጵያ ........ 20
የኤጲስ ቆጶሳት አመራረጥ ሥርዓት ........ 27
ለኤጲስ ቆጶስነት የሚያበቁ መስፈርቶች ........ 29
የቅዱስ ሲኖዶስ ትርጓሜ ........ 30
ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ........ 32
ወደ ከተማ ውጭ እንውጣ ........ 36
የመጨረሻው አንቀጽ ........ 40
የማንታወቅ ይምስለን እንጂ ብዙዎች ያውቁናል ........ 47
‹‹የውጫሌው ውል›› ........ 50
ብፁዓን ናችሁ ........ 51
ሙስና ነክ ቅኔዎች ........ 53


# መ ቅ ድ ም

**‹‹በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለባት ኅሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ›› (ሐዋ. 24፥16)**

‹‹ምንዙስና በኢትዮጵያ ዛሬና ትናንትና›› የሚለው መጽሐፌን ካነበቡ ሰዎች አንዳንዶቹ በስልክና በግንባር ‹‹የማይነካውን እንዴት ደፍረህ ነካህ?›› ሲሉ አድናቆት በተቀላቀለበት ስሜት ጠይቀውኛል። ከእነዚህ ሰዎች ጥያቄና አስተያየት የተገነዘብኩት ነገር ቢኖር ዘመናችን ከእውነት ይልቅ ሐሰት ያየለበት፣ አድርባይነት የተስፋፋበት፣ መንፈሳዊ ሕይወት በዓለማዊ ኑሮ የተዋጠበት ጊዜ መሆኑን ነው።

በመሠረቱ እኔ ከኅሊናየ አፍልቄ አዲስ ነገር አልጻፍኩም፤ አበው ሊቃውንት ጽፈው ካወረሱን፣ መምህራን ቀምረው ካስቀመጡልን ቆንጥሬ አቀረብኩኝ እንጂ። ደግሞ እኮ እውነትን መመስከር አያስፈራም፣ አያሳፍርም። እንደእውነቱ ከሆነ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ለእውነት፣ ለፍትሕና ለሃይማኖታቸው ሲሉ ደማቸውን ያፈሰሱ፣ እጅ እግራቸው በሰይፍ የተቆረጡ፣ ገደል ተጥለው የአሞራና የአውሬ ሲሳይ የሆኑ፣ ነበልባለ እሳት ውስጥ ተጥለው እንደ ጧፍ የነደዱ፣ ቀያቸውን ጥለው የተሰደዱ፣ በአጠቃላይ አኩሪ ገድል ፈጽመው ባለፉባት አገር እንዲት የእውነት ጠብታ ቀለም ማስፈር እንደብርቅ ማየት ባልተገባ ነበር።

በበኩሉ ብላታ ወ/ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ በ1945 ዓ.ም ባሳተሙት ‹‹አምስት መንገደኞች በገነ፡ ምዕራፍ ላይ›› በሚለው መጽሐፋቸው

‹‹ፍርሃት ለጽሕፈት ገንዘቡ አይደለም፣ የብዕር አፍንጫ የሸተተውን ሙትንፈስ አሰበት›› እንዳሉት ዛሬም ቢሆን ነገ የብርዔ አፍንጫ የሸተተው መጻፌን እቀጥልበታለሁ። ነቢዩ ዳዊት፦ ‹‹አቤቱ የሚጠሉህን እኔ የጠላሁ አይደለሁምን?›› (መዝ. 138፥21) እንዳለው በቤተ ክርስቲያን ስም የሚነግዱትን፣ ለቤተ ክርስቲያን መኖር ሲገባቸው በቤተ ክርስቲያን የሚኖሩትን ከመዋጋት ወደ ኋላ አልልም። እንዲህ በማድረጌም እግዚአብሔር በቀኜ እንደሚቆም አልጠራጠርም።

እንደ ‹‹ምንዝስና በኢትዮጵያ›› ሁሉ ይህ መጽሐፍም ወቅታዊ ነው የሚል እምነት አለኝ። በተረፈ አንባቢዎች ከዚህች አነስተኛ መጽሐፍ ስለ ብፅዕና ሰፋ ያለ ግንዛቤ ያገኛሉ የሚል ተስፋ አለኝ። እስከ አሁን ባለው ሁኔታ ለመታዘብ እንደቻልኩት ብዙዎች ምእመናን ‹‹ብፁዕ›› የሚለውን ቃል ሲሰሙ ወይንም ሲያነቡ በቀጥታ የሚያያይዙት ከሊቃነ ጳጳሳት ጋር ብቻ ነው። የዚህ መጽሐፍ አንዱ ዓላማ የቃሉ ትርጉም ከዚህም የሰፋ መሆኑን ለማሳየትና ‹‹እኛ ብቻ ነን ብፁዓን›› የሚሉ ካሉም አለመሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ አድርጌ ልሞግታቸውና ብፅዕና በሥራ እንጂ በሹመት የማይገኝ መሆኑን ለማሳየት ስለፈለግኩኝ ነው።

በመጨረሻም ለጽሑፌ በማጣቀሻነት የተጠቀምኩባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በተለያዩ ጊዜያት ከታተሙ እትሞች የተወሰዱ በመሆናቸው አልፎ አልፎ የሚታዩ የምዕራፍና የቍጥር ልዩነቶች ከዚህ አንጻር የተከሰቱ መሆኑን አንባብያን እንዲትገነዘቡልኝ እፈልጋለሁ።

‹‹በእግዚአብሔር ሕመንኩ ሕልፈራም፣ ሰው ምን ያደርገኛል?››

(መዝ. 55፥11)



# ብፁዓን እነ ማን ናቸው?

## ‹‹ጻድቃን ሁሉ ብፁዓን ናቸው›› (ሄኖ. 28፥5)።

**ብፁዕ፦** ‹‹የታመነ፣ የተመሰገነ፣ ሥራውና ልቡ የቀና፣ ክቡር፣ ምስጉን፣ ምሩቅ፣ ብሩክ፣ ቅዱስ፣ ጻድቅ፣ ቸር፣ ብእሴ እግዚአብሔር››[1] ማለት ነው። ብፁዕ ደስተኛ[2] ማለትም ይሆናል። እንደ አለቃ ኪዳነ ወልድ አባባል ብፁዕ የሚለው ቃል ስምነቱ ማእከላዊ ሆኖ ከንጹሕ በላይ ከቅዱስ በታች፣ ለወጣኒና ለፍጹም ለኹሉ የሚሆን ነው። በመሆኑም ፈጣሪ ሳይቀር ብፁዕ ተብሏል።

‹‹ስብፁዕ እግዚአብሔር = የብሩክ እግዚአብሔር›› (1ጢሞ. 1፥11)

‹‹ወብሩክ አምላኪየ = አምላኬም ብሩክ ነው›› (መዝ. 17፥46)

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ብፅዕት በሚለው የክብር ስም ትጠራለች።

‹‹መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ ደስ ይበልሽ፣ ጸጋንም የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ፣ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው፣ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ <u>የተባረክሽ</u> ነሽ›› አላት (ሉቃ. 1፥28፥42)።

‹‹ከእግዚአብሔር ዘንድ የነገረሽ ቃል እንደሚሆን የምታምኚ አንቺ <u>ብፅዕት</u> ነሽ›› (ሉቃ. 1፥45)።

‹‹ቅድስት <u>ወብፅዕት</u> ስብሕት ወቡሩክት = ቅድስት ሆይ <u>ብፅዕት</u> ነሽ።››

‹‹አስተማስልናኪ ቅድስት <u>ወብፅዕት</u> = የተለየሽና ደግ የሆንሽ <u>የተመሰገንሽ</u>›› (ቅዱስ ያሬድ፡ አንቀጸ ብርሃን)

ብፁዕ ለሚለው ቃል ዘርፈ ብዙ ትርጉም በመስጠትና ደጋግሞ በመጠቀም በኩል ነቢዩ ዳዊት ተወዳዳሪ የለውም። ሌላው ቢቀር

[1] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፦ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ፦ 1945 ዓ.ም

[2] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፦ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት 8ኛ እትም

መዝሙሩን የጀመረው ስለጻድቃንና ኀጥአን ማንነትና ትርጉም በመስጠት ነው፡፡

‹‹ምስጉን ነው በዝንጉዎች[3] ምክር ያልሄደ በኀጢአተኛም መንገድ ያልቆመ በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ ሰው፡፡ የእግዚአብሔር ሕግ ብቻ ፈቃዱ የሆነ ሕጉንም በቀንና በሌሊት የሚያስብ እርሱም በውሃ ፈሳሾች ዳር እንደተተከለች ፍሬዋን በየጊዜው እንደምትሰጥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል (መዝ. 1፥1-3)፡፡

ነቢዩ ኤርምያስም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ሐሳብ ሰንዝሯል፡፡

‹‹በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ብሩክ ነው፡፡ በውሃ አጠገብ እንደተተከለ፣ በወንዝም ዳር ሥሩን እንደሚዘረጋ፣ ሙቀትም ሲመጣ እንደማይፈራ ቅጠሉም እንደሚለመልም፣ በድርቅ ዓመትም እንደማይሰጋ፣ ፍሬውንም እንደማያቋርጥ ዛፍ ይሆናል›› (ኤር. 17፥7-8)፡፡

ዳዊት በመቀጠል በእግዚአብሔር አደባባይ፣ ቤትና ድንኳን የሚኖሩ ብፁዓን መሆናቸውን ከመሰከረ በኋላ (መዝ. 64፥4፣ 111፣ 1-2) በእግዚአብሔር ቤት መኖር የሚችሉት (የሚፈቀድላቸው) እነማን እንደሆኑ በሚከተለው መንገድ ያስቀምጠዋል፡፡

‹‹አቤቱ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል?
በተቀደሰው ተራራህ ማን ይኖራል?
በቅንነት የሚሄድ፣ ጽድቅንም የሚያደርግ
በልቡም እውነትን የሚናገር፡፡
በአንደበቱ የማይሸነግል፣
በባልንጀራው ላይ ክፋትን የማያደርግ
ዘመዶቹንም የማይሰድብ፡፡
ኀጢአተኛ በፊቱ የተናቀ፣
እግዚአብሔርንም የሚፈሩትን የሚያከብር፣
ለባልንጀራው ምሎ የማይከዳ፡፡

[3] ‹‹ምናምንቴዎች›› ማለትም ይሆናል፡፡



ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር፣
በንጹሑ ላይ ማማለጃን የማይቀበል፤
እንዲህ የሚያደርግ ለዘለዓለም አይታወክም›› (መዝ. 14፥1-5፣ 23፥3-5፣ ኢሳ. 33፥15-16)፡፡

በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ በጎ ነገርን የሚያዩ ብፁዓን መሆናቸውና ይህን ለማግኘት መደረግ ስላለበት ሲያስረዳም፡-

‹‹ሕይወትን የሚፈቅድ ሰው ማነው?
በጎም ዘመን ለማየት የሚወድ?
አንደበትህን ከክፉ ከልክል
ከንፈሮችህም ሽንገላ እንዳይናገሩ፡፡
ከክፉ ሽሽ መልካምንም አድርግ፣
ሰላምን እሻ ተከተላትም›› (መዝ. 33፥12-14) በማለት ይገልጻል፡፡

በሌላ በኩል ዳዊት እግዚአብሔርን የሚፈሩና ትእዛዙን በማክበር በመንገዱ የሚሄዱትን ብፁዓን ይላቸዋል፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈሩና በመንገዱ የሚሄዱ ሰዎች ስለሚያገኙት ክብርና ጸጋም እንዲህ በማለት ይዘረዝራል፡፡

‹‹ዘሩ በምድር ላይ ኃያል ይሆናል፣ ክብርና ባለጠግነት በቤቱ ነው፤›› (መዝ. 111፥1-3)፡፡

‹‹የድካሙን ፍሬ ይመገባል፣ ሚስቱ በቤቱ ውስጥ እንደሚያፈራ ወይን ትሆናለች፣ ልጆቹም በማዕዱ ዙሪያ እንደ አዲስ የወይራ ተክል ይሆኑለታል›› (መዝ. 127፥1-3)፡፡

ዳዊት ብፁዓንን አስመልክቶ ካሰፈራቸው ተጨማሪ መልእክታት የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡፡

‹‹ወደ ከንቱ ነገር፣ ወደ ቁጣና ወደ ሐሰትም ያልተመለከተ ሰው ብፁዕ ነው›› (መዝ. 39፥4)፡፡

‹‹ለድሃና ለምስኪን የሚያስብ ብፁዕ ነው›› (መዝ. 40፥1)፡፡

‹‹እልልታን የሚያውቅ ሕዝብ ብፁዕ ነው›› (መዝ. 88፥15)።
‹‹እግዚአብሔር አምላኩ የሆነለት ሰው ብፁዕ ነው›› (መዝ. 32፥112)።
‹‹ምክሩን የሚፈልጉ በፍጹም ልብ የሚሹት ብፁዓን ናቸው›› (መዝ. 118፥2)።
‹‹በአንተ የታመነ ሰው ብፁዕ ነው›› (መዝ. 33፥8)።

## የብፁዓን ተምሳሌቶች

ዓለማችን እልፍ አእላፋት ብፁዓን አፍርታለች፣ አሁንም ማፍራትዋን ቀጥላበታለች፣ ይህ ሂደት እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ይዘልቃል። በመሆኑም የሁሉም ብፁዓን ስምና ተግባር መዘርዘር ከዋክብትን ለመቍጠር የመሞከር ያህል ይሆናል። አለቃ ኪዳን ወልድ ክፍሌ ‹‹ብፁዕ›› ለሚለው ቃል ትርጕም በሰጡበት ጽሑፋቸው በምሳሌነት የጠቀሱአቸው አብርሃም፣ ኢዮብና ዳዊትን ነው። እኛም እነዚህን በተምሳሌነት በመጠቀም ስለእያንዳንዳቸው ትንሽ እንበል።

### አብርሃም

መጽሐፍ ‹‹በእኔ የማይጠራጠር ሁሉ ብፁዕ ነው›› (ማቴ. 11፥6) እንዳለ አብርሃም እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ ማምለክ የጀመረውና ወጣት እያለ ነበር። አብርሃም እግዚአብሔር የነገረውን ሳይጠራጠር በፍጹም ልቡ በመቀበል የአባቱን ጣዖታት በእሳት በማቃጠል፣ አባቱን፣ ዘመዶቹንና የትውልድ ቦታውን በመተው ወደ ከነዓን ምድር ተጓዘ፤ በእግዚአብሔር በማመኑም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት (ዘፍ. 15፥6፣ ኩፋ. 12፥4)።

አብርሃም በእምነቱ የድርቅና የረሀብ ፈተናን አልፎአል፣ በነገሥታት ገንዘብ ተፈትኖ አልፎአል፣ በሚስቱ መቀማት ተፈትኖ አልፎአል፣ በመገረዝ ተፈትኖ አልፎአል። እርሱ መቶ ዓመት ሚስቱ ሣራ ዘጠና ዓመት ከሆናቸው በኋላ እግዚአብሔር ‹‹ይስሐቅ የሚባል ወንድ ልጅ



ትወልዳለችሁ... ልጅህንም እባርከዋለሁ፣ አበዛዋለሁ›› ሲለው እኔና ሚስቴ ሸምግለናልና እንዴት መውለድ እንችላለን? በማለት አልተጠራጠረም፣ እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ እንደሚቻለው አምኖ ተቀበለ እንጂ (ዘፍ. 17፥15-21)።

ይስሐቅ ካደገ በኋላም እግዚአብሔር አብርሃምን ሲፈትነው ‹‹አንድ ልጅህን ይስሐቅን ሠዋልኝ›› ሲለው (ዘፍ. 22፥1-2) አንድ ልጄን ወራሼን፣ ተተኪየን እንዴት አድርጌ? አላለም። በፍጹም እምነትና ታዛዥነት ልጁን ለመሠዋት ካራውን አነሣ እንጂ፤ በዚህ በተግባር በተፈተነ ጠንካራ እምነቱም ሰይጣንን አሳፍሮአል (ኩፋ. 14፥13)።

አብርሃም ለጋስና ለድሃ የሚያስብ ሰው ነበር። መጽሐፍ፡-

‹‹ለድሃና ለምስኪን የሚያስብ ብፁዕ ነው›› (መዝ. 40፥1) እንዲል። አብርሃም ለጋስና ቸር ከመሆኑ የተነሣ ወደ ቤቱ እንግዳ ካልመጣ ብቻውን ማዕድ አቅርቦ አይበላም ነበር። በዚህ የጽድቅ ተግባሩም ሥላሴን ለመጋበዝና ለመባረክ በቃ። አብርሃም ጥዋት ጥዋት እየተነሣ ሁሉን ለፈጠረ አምላኩ ለእግዚአብሔር እየተገዛ ያመሰግንም ነበር (ኩፋ. 13፥22)። በአጠቃላይ አብርሃም በጽድቅ ተግባሩ እግዚአብሔር ‹‹እኔ ላንተ ጋሻ ነኝ›› ብሎታል (ዘፍ. 15፥1፣ ኩፋ. 12፥1)። የእግዚአብሔር ወዳጅ (አርከ እግዚአብሔር) ያሰኘውም ይህ ሁሉ ተደማምሮ ነው።

### ኢዮብ

**ኢዮብ፡-** ‹‹ፍጹምና ቅን፣ እግዚአብሔርም የሚፈራ ከክፋትም የራቀ ነበረ›› (ኢዮ. 1፥1)።

‹‹ዘወትር ግስዳ እየተነሣ በራሱና በልጆቹ ስም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የሚያቀርብና የሚጸልይ ጻድቅ ሰው ነበረ›› (ኢዮ. 1፥5)።

‹‹መከራ የሚታገሥ ሰው ብፁዕ ነው›› (ያዕ. 1፥12)።

‹‹በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን›› (ያዕ. 5፥11)፡፡

‹‹ወደ እናንተ ከሚላኩ ጠላቶች ብትታገሱ ብፁዓን ትሆናላችሁ›› (3መቃ. 8፥4)፡፡

በተባለው መሠረት በመከራና በተለያየ ስቃይ ሊፈትነው የመጣውን ሰይጣን በትዕግሥቱ ድል ያደረገ ብፁዕ ሰው ነበረ፡፡ በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ይበልጥ አከበረው፡፡

‹‹ኢዮብ በእግዚአብሔር አመነ፣ ፈጣሪው እግዚአብሔር ማመስገንን ቸል አላለምና የአዳም ልጆች ጠላት ዲያብሎስ ካመጣበት መከራውም ሁሉ አዳነው፤ በደረሰበትም መከራ ልቡን አላሳዘነም፣ ነገር ግን ‹‹እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚአብሔርም ነሳ፣ እግዚአብሔርም እንደወደደ ሆነ፤ በሁሉም በሰማይና በምድር የእግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን›› አለ፡፡ እግዚአብሔርም የኢዮብ ልቡ ንጽሕት እንደሆነች ባየው ጊዜ፣ እግዚአብሔር በብዙ ክብር ተቀበለው›› (3መቃ. 8፥1-2)፡፡

## ዳዊት

ዳዊት ገና በእናቱ ሆድ እያለ በእግዚአብሔር የተመረጠ፣ (መዝ. 21፥10) ገና ወጣትና የበግ እረኛ እያለ እግዚአብሔር ለንግሥና የጠራው (የቀባው)፣ የእግዚአብሔር ታዛዥና ዘወትር በጽድቅ መንገድ የሚጓዝ፣ ‹‹ፈቃዴን ሁሉ የሚፈጽም እንደልቤም የታመነ ሰው ሆኖ አገኘሁት›› በማለት እግዚአብሔር የመሰከረለት ሰው ነበር (1ሳሙ. 16፥12-13 ሐዋ. 13፥22)፡፡

እግዚአብሔር ሳሙኤልን ‹‹ከእሴይ ልጆች መካከል ንጉሥ የሚሆን አዘጋጅቻለሁና ሂደህ ቀባው›› ባለው ጊዜ በመጀመሪያ ሊቀባ የፈለገው ኤልያብን ነበር፤ ኤልያብ በቁመቱ ዘለግ ያለ ነበርና፤ እግዚአብሔር ግን ‹‹አንተ ያየኸው ፊቱን ነው፣ ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያልና አሳልፈው አለው፤ በዚህ መልክ ሰባቱ የእሴይ ልጆች በሳሙኤል ፊት አለፉ፣ እግዚአብሔር ግን ከሰባቱ አንዳቸውንም ሳይመርጥ ቀረ፡፡ በዚህን ጊዜ ሳሙኤል እሴይን፦ ‹‹እግዚአብሔር



እነዚህን አልመረጠምና የቀረ ሌላ ልጅ አለህ ወይ?›› በማለት ጠየቀው፡፡

**እሴይም፦** ‹‹ታናሹ ገና ቀርቶአል፤ እነሆም በጎችን ይጠብቃል›› አለ፡፡ ሳሙኤልም ‹‹እንግዳው እሱን አስመጣው›› አለ፡፡ ዳዊት እንደመጣ እግዚአብሔር ሳሙኤልን፦ ‹‹ይህ ነውና ተነሥተህ ቀባው›› አለው፡፡ ሳሙኤልም ተነሥቶ በወንድሞቹና በአገሩ ሽማግሌዎች ፊት ቀባው፤ ከዚያች ሰዓት ጀምሮም በዳዊት ላይ መንፈስ ቅዱስ አደረበት፣ ኃይልም መጣለት (1ሳሙ. 16፥1-13)፡፡

ከዚህ የምንረዳው ዳዊት ልቡ ንጹሕ ውስጡ ሩኅሩኅ እንደነበረ ነው፡፡ ‹‹ወዳዊትኒ ኮነ ትሑተ = ዳዊትም ትሑት ነበረ›› እንዲል (ፊልክ 1)፡፡ ዳዊት ራሱ ‹‹እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን በጎ ነገር አታሳጣቸውም (መዝ. 24፥11) እንዳለ እግዚአብሔርን አምኖ አካሄዱን በማስተካከሉ ገና በሕጻንነቱ አስፈሪና ኃይለኛ የነበረው ጎልያድን ድል ሊመታው ቻለ፡፡ ከነገሠ በኋላም ፍልስጥኤማውያንን፣ ሞዓባውያንን፣ ሶርያውንን፣ ኤዶማውያንን፣ አሞናውያንን ለማቸነፍ ቻለ፡፡

ዳዊት ንጉሥና ኃያል ቢሆንም ቂም በቀል የማያውቅ የይቅርታ ሰው ነበረ፡፡ ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ያላደረገው ጥረት አልነበረም፤ ይሁን እንጂ ዳዊት ከአንዴም ሁለቴ ሳኦል በእጁ ገብቶለት እያለ ‹‹እግዚአብሔር የቀባውን አልገድልም›› በማለት በርኅራኄ ዓይን በማየት ትቶታል (1ሳሙ. 24፥4-7፣ 26፥6-12)፡፡ ዳዊት በእስራኤል ላይ ለዐርባ ዓመታት የነገሠ፣ በዙሪያው የነበሩ ጠላቶቹን ድል በማድረግ ሕዝቡን በሰላም መንገድ የመራ ቢሆንም ንጉሥ ነኝና ያማረኝን ልብላ፣ ልጠጣ አይልም ነበር፡፡ ይልቁንም አዘውትሮ ሰውነቱን በጾም ያደክም ነበር እንጂ (መዝ. 34፥13)፡፡

ዳዊት ሰው እንደመሆኑ አልፎ አልፎ እግዚአብሔርን ያስቀየመባቸው ጊዜያትም ነበሩ፡፡ ከሁሉ የበለጠውን በደል ቤርሳቤህን

የራሱ ለማድረግ የጦር ቧለሟሉ ኦርዮንን ማስገደሉ ነበር። ዳዊት በጊዜያዊ ስሜት ተነሣሥቶ ይህን በደል ቢፈጽምም በመጨረሻ ከልብ በመነጨ ስሜት እግዚአብሔርን ይቅርታ በመጠየቁና ንስሐ በመግባቱ እግዚአብሔር ይቅርታ አደረገለት።

‹‹በልቤስ በደልን አይቶ ቢሆን እግዚአብሔር አይሰማኝም ነበር›› (መዝ. 65፥18) እንዳለ። በመሆኑም ኢዮብ በትዕግሥቱ፣ አብርሃም በእምነቱ ብፁዓን እንደተባሉ ሁሉ ዳዊት በተነሳሒነቱ ብፁዕ ተባለ።

‹‹መተላለፋቸው የቀረላቸው፣ ኃጢአታቸውም የተሰረየላቸው ብፁዓን ናቸው። እግዚአብሔርም በደሉን የማይቆጥርበት ሰው ብፁዕ ነው›› (ሮሜ. 4፥7-8፣ መዝ. 32፥1-2) ተብሏልና።

## ሐዋርያትና ብፅዕና

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጀመሪያ ጊዜ ብፁዕ የሚለውን ቃል የጠቀሰው በተራራው ስብከቱ ነበር (ማቴ. 5፥3-14)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ብፅዕና ያስተማረው ለሕዝቡና ለሐዋርያቱ በአንድነት ቢሆንም በዋናነት ያተኮረው በሐዋርያት ላይ መሆኑን ከሰጠው ትምህርት መረዳት ይቻላል፤ እንዲህም አለ፦

‹‹በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፣ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና (ማቴ. 5፥3፣ ኢሳ. 57፥15)።

የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፣ መጽናናትን ያገኛሉና (ማቴ. 5፥4፣ መዝ. 127፥5፣ ኢሳ. 61፥2፣ ራዕ. 7፥17)።

የዋሆች ብፁዓን ናቸው፣ ምድርን ይወርሳሉና (ማቴ. 5፥5፣ መዝ. 37፥11)።

ስለጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ ይጠግባሉና (ማቴ. 5፥6፣ ኢሳ. 41፥17፣ 50፥1-2)።

የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፤ ይማራሉና (ማቴ. 5፥7፣ ያዕ. 2፥12)።

ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና (ማቴ. 5፥8፣ 1ዮሐ. 3፥2-3)።



የሚያስታርቁ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና (ማቴ. 5፥9፣ ዕብ. 12፥14፣ መዝ. 34፥15)።

ስለጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፣ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና (ማቴ. 5፥10፣ 1ጴጥ. 3፥14፣ 2ጢሞ. 2፥12)።

ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ›› (ማቴ. 5፥11-12፣ 1ጴጥ. 4፥14፣ ኢሳ. 51፥7-8)።

በእርግጥም ጌታችን መድኃኒታችን እንዳስተማረው ሐዋርያት ብፁዓን ነበሩ። ሐዋርያት በጨውና በብርሃን የተመሰሉትም ለዚሁ ነው (ማቴ. 5፥13-14፣ ማር. 9፥50፣ ሉቃ. 14፥34፣ ዮሐ. 8፥12 ፊል. 2፥15)። ሐዋርያት ‹‹የዓለም ወዳጅ የእግዚአብሔር ጠላት ነው›› (ያዕ. 4፥14) የሚለውን አምላካዊ መርህ በመከተል ዓለምን ላለመምሰል ወስነው ሰማያዊ መንገድን መርጠው ደቀ መዛሙርቱ ሆኑ (ሮሜ. 12:2)።

‹‹ስለ ስሜ ቤትን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም ርስትን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ዋጋ ያገኛል፤ የዘለዓለም ሕይወት ይወርሳል (ማቴ. 19፥27-30፣ ዕብ. 10፥34) ሲል ባስተማራቸው መሠረት ሁሉን ትተው ተከተሉት (ማር. 10፥28)።

ራስን ዝቅ አድርጎ ለሌላ መታዘዝ (ማገልገል) ብፅዕና መሆኑን ለማሳየት ጌታችን ወገቡን ታጥቆ የሐዋርያትን እግር ካጠበ በኋላ፦ ‹‹እናተም እንዲህ ብታደርጉ ብፁዓን ናችሁ›› ብሎ በተግባር ያሳያቸውን የትሕትና አብነት መሠረት በማድረግ ለምእመናንና ለተከታይ ደቀ መዛሙርቶቻቸው አርአያ ሆኑ (ዮሐ. 13፥17-18)።

እርሱ እንደወደዳቸው ሁሉ እርስ በርሳቸው ተዋደዱ፤ ስለጽድቅ ብለው ተራቡ፤ የሚበድልዋቸውን፣ የሚገርፉአቸውን፣ ይቅር በማለት ልበ ንጹሕነታቸውን በተግባር አሳዩ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን በመስበካቸው፣ በስሙ ሕሙማንን በመፈወሳቸው፣ አጋንንትን በማውጣታቸው ምክንያት

ይደርስባቸው የነበረውን ስቃይ፣ ስደት፣ ግርፋትና እስራት በጸጋ በመቀበል በጨለማ ዓለም ይኖሩ ለነበሩ ሁሉ የመስቀሉ ብርሃን እንዲደርሳቸው አደረጉ።

የሐዋርያት ብፅዕና በተነሣ ቊጥር የሚወሳ አንድ ቁም ነገር አለ፤ ይኸውም የቅዱስ ጴጥሮስ የብፅዕና ሢመት ነው። ጌታችን «የሰውን ልጅ ሰዎች ማን ይሉታል?» በማለት ሐዋርያትን በጠየቀበት ጊዜ-ቅዱስ ጴጥሮስ «አንተማ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ» አለው። ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፡-

«የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ አንተ ብፁዕ ነህ... እኔም እልሃለሁ አንተ ዐለት ነህ፤ በዚች ዐለት ላይም ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ፤ የሲኦል በሮችም አይበረታቱባትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ» (ማቴ. 16፥13-19፣ ኤፌ. 2፥20)።

በማለት ተጨማሪ የብፅዕና ማዕረግ ሰጠው። በዚህም ቅዱስ ጴጥሮስ ርእሰ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ አሠረ ክህነቱን ለተከተሉ ሁሉ ተምሳሌት በመሆን እስከ ዘለዓለም ስሙ ሲወሳ ይኖራል።

እስከ አሁን ለማየት እንደሞከርነውና በመጽሐፈ ሄኖክ እንደ ሰፈረው ብፅዕና የጻድቃን ሁሉ መገለጫና መለያ ነው። በአጠቃላይ ሴትም ይሁን ወንድ፣ ወጣትም ይሁን አዛውንት፣ የእግዚአብሔርን ሕግጋትና ትእዛዛት አክብሮ ሕይወቱን በቅድስና ጐዳና መምራት የቻለ ሁሉ ብፁዕ ነው (ይሆናል) ማለት ነው።

> «ፍጻሜውን ሳታይ ሰውን ብፁዕ አትበለው (ሲራ. 11፥28)



# ኢትዮጵያውያንና ብፅዕና

ታሪክ እንደሚያስረዳን ብፅዕና ለዘመናት የኢትዮጵያውያን መለያ በመሆን አገልግሏል። «ማን ይናገር የነበረ...» ነውና እንደ ኢትዮጵያ ጥንታዊ የሥልጣኔ መሠረት የነበራቸው ፐርሺያውያንና ግሪካውያን ይህንን በጽሑፎቻቸው በማስፈር ማንነታችንን ለተቀረው ዓለም አሳውቀውልናል፤ እስቲ ለአብነት አንድ ሁለቱን ቀንጭበን እንይ።

ሄሮዶተስ ኢትዮጵያውያንን «በምድር ላይ እጅግ ያመረ ደም ግባት ያላቸው የተዋቡ ሕዝቦች ናቸው» ካለ በኋላ «ርኅራኄያቸው እንደ እግዚአብሔር፣ ቸሮች፣ ለመንገደኛ ሁሉ ድግስ እየደገሱ ኑ ብሉልን፣ ጠጡልን እያሉ የሚያስተናግዱ፣ ...በሕግና በሥርዓት መኖርን የሚወዱ፣ ነውርና ክፉ ነገር በሀገራቸው የተጠላና የተጸየፈ ...» በማለት ይገልጻቸዋል።[4]

ፐርሺያውያንም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ጽሑፍ ጽፈው ለታሪክ ትተዋል። በጥንታዊው የፔርሴፖሊስ ቅርጽ ስለ ኢትዮጵያ ከተጻፈው ውስጥ፡-

> «ኢትዮጵያውያን ኩሩ በነበሩ የጨዋ ወገኖች የሚመሩ፣ ለነፃነታቸው ቀናተኞች የሆኑ... ወርቅና የቀንድ ከብት የሞሰባት ሀገር ያሰቻቸው፣ ማር ወተትና ሥጋ እንደፈለጉት የሚያገኙ... ዕድሜያቸው ከ120 ዓመት በላይ የሆነ፣ ንጉሣቸው ቁመቱ ረዥም፣ አቋሙ ትክክል የሆነ፣ ከሕዝቡ ዘንድ የተከበረና የታፈረ...»

የሚል ኃይለ ቃል ሰፍሮ ይገኛል። በማከልም፡-

> «ሕዝቡ ለመንገደኞችና ለእንግዶች ከሚያደርገው ነፃ መስተንግዶ በተጨማሪ ንጉሡ ከመናገሻው (አክሱም) ከተማ ዳር «የፀሐይ ገበታ» የሚባ ስያሜ ያለው ማስተናገጃ ቦታ አለው፣ በዚህ ገበታ ሌሊትና ቀን የተሰናዳ ምግብ ስለሚገኝ ለጉዳይ ወደ ከተማ የመጣ ሰው፣ መንገደኛና ደሃ ባሻው ሰዓት እየመጣ ከማዕዱ ይሳተፋል»[5]

[4] ፍስሐ ጽዮን ካሣ (መምህር) መርኖ- 1983 ዓ.ም ገጽ 9

[5] DARLUS AT SUSA:- Kahyn International (Sep. 14,1964)

በማለት ጥንታውያኑ የፋርስ ሰዎች ጽፈዋል።

ታቦተ ጽዮንን ይዞ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ካህኑ አዛርያስም አኩሱም እንደገባ የሰጠው ምስክርነት የሀገሪቱን ቅድስናና የሕዝቦቿን ብፅዕና የሚያረጋግጥ ነበር። ካህኑ አዛርያስ ከሰጠው ሰፊ ምስክርነት እንዲህ የሚል ይገኝበታል።

‹‹ከቀደሙት አባቶቻችን ጀምሮ እስከ እኛ ድረስ ከያዕቆብ ጀምሮ እግዚአብሔር እኛን የሱ ዘሮች አድርጎ መረጠን፣ እኛንም አብዝቶ ቤተሰቡ አደረገን፣ ወደደን፣ አነገሠን፣ ባለሟሎቹ አደረገን፣ ለእኛ ብቻ የኪዳኑን ታቦት ሰጠን፣ ከሀገሮች ሁሉ የእኛን ሀገር መረጠ እንል ነበር፤ ዛሬ ግን ከሀገረ ይሁዳ የምትበልጥ ሀገር ኢትዮጵያን በዓይናችን አየን፤ ወደ ሀገራችሁ ከደረስን ጀምሮ ባየነው ሁሉ ተደነቅናል። ተፈጥሮው እጅግ የማይደረስ ነው፣ ጥሩ ውሃ አላችሁ፣ አየሩ (ነፋሱ) ሕይወትን ያድሳል፣ የማር ወለላ እንደዚህ የተትረፈረፈበት እስከ አሁን አላየንም፣ አልሰማንም፣ የሀገሩ እንስሳት እንደ ባሕር አሸዋ የበዙ ናቸው፤ የረገጥነው ምድር ሁሉ ቅዱስ ነው፤ የሚበላውና የሚጠጣው ሁሉ ለጤና ተስማሚና ጣፋጭ ነው። እግዚአብሔር በነቢያት አድሮ ሕዝበ እስራኤልን እንደሚንቅና ከሕዝበ እስራኤል ውጭ ሌሎች ሕዝቦችን እንደሚያስነሣ የተናገረው በተግባር ሲፈጸም አየነው።››**

ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣትዋ በፊትም ንግሥተ ሳባ የፈጸመችው የብፅዕና ተግባር እዚህ ላይ የሚጠቀስ ነው። ንግሥተ ሳባ ከባለሟልዋ ነጋዴ ታምሪን የሰማችው የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብ ለመቅሰም ወደ ኢየሩሳሌም በሄደችበት ጊዜ ቀዳማዊ ምኒልክን አርግዛ ተመለሰች። ይህም የኋላ ኋላ ለታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ምክንያት ሆነ። ከዚህም በላይ ንግሥተ ሳባ በሕይወት ዘመንዋ ከፈጸመችው ቅዱስ ተግባር ሌላ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ እንደሚገኘው በፍርድ ቀን ከጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጐን ቆማ በክብር እንደምትገለጥ ያሳያል (ሉቃ. 11፥31)

**ታቦተ ጽዮን በኢትዮጵያ ጥር 2001 ዓ.ም ገጽ 36



የእስራኤላዊው ንጉሥ ሴዴቅያስ ባለሟልና የነቢዩ ኤርምያስ ወዳጅ የነበረው ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ከብፁዓን ወገን የሚደመር ነው። አቤሜሌክ ንጉሡ ለተበደሉ ምሕረትና ፍትሕ እንዲሰጥ በማማከር የላቀ አስተዋጽኦ ያደርግ ነበር። ነቢዩ ኤርምያስ ከፈጣሪው በታዘዘው መሠረት፦ ‹‹ኢየሩሳሌም ትፈርሳለች፣ ሕዝቡም በሰይፍና በራብ፣ በቸነፈርም ይሞታል... ይህች ከተማ በባቢሎን ንጉሥ ሠራዊት እጅ በርግጥ ትሰጣለች፣ እርሱም ይይዛታል (ኤር. 38፥2-3)›› ብሎ በመናገሩ በንጉሡ አደባባይ ግዞት ቤት ወደነበረው መልክያ ጉድጓድ በጣሉት ጊዜ አቤሜሌክ ንጉሡን ለምኖ ኤርምያስን አስወጣው።

በትንቢቱ መሠረት የኢየሩሳሌም መጥፋት በተቃረበ ጊዜ እግዚአብሔር ነቢዩ ኤርምያስን ለአቤሜሌክ፦

‹‹እነሆ ለበጎነት ሳይሆን ለክፋት ቃሌን በዚች ከተማ ላይ አመጣለሁ፤ በዚያም ቀን በፊትህ ይፈጸማል። በዚህም ቀን አድንሃለሁ ይላል እግዚአብሔር፤ ከፊታቸውም የተነሣ በምትፈራቸው ሰዎች እጅ አልሰጥህም፤ ፈጽሜ አድንሃለሁ... በእኔ ታምነሃልና›› (ኤር. 39፥16-17) ብለህ ንገረው ብሎታል።

ነቢዩ ኤርምያስ በበኩሉ በኢየሩሳሌም ጥፋት ዋዜማ ከእግዚአብሔር በተነጋገረበት ወቅት አቤሜሌክን አስመልክቶ እንዲህ በማለት ፈጣሪውን ተማጽኖ ነበር።

‹‹ጌታዬ ሆይ እለምንሃለሁ፣ ሕዝቡን ብዙ ዘመን ለጠበቃቸው፣ እኔን ባርያህ ኤርምያስንም ከሀገሩ ሰው ሁሉ ይልቅ ለጠበቀኝ ለኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ የማደርገውን ግለጥልኝ። እርሱ ከረግረግ ጉድጓድ አወጣኝ፣ እንዳያዝን የከተማዋን ጥፋት ያይ ዘንድ አልወደድለትም›› (ተ.ባ.2፥8-9፤ ተ.ኤ.8፥8)።

ጌታም የኤርምያስን ልመና ተቀብሎ አቤሜሌክን በግሪጳስ ወይን ቦታ ለ66 ዓመታት ሰውሮ አስቀመጠው (ተ.ባ.2፥10፤ ተ.ኤ.8፥9)።

አሁን ደግሞ ወደ ዘመነ ሐዲስ እንምጣና በተመሳሳይ አንድ ሁለት ማስረጃዎችን እንመልከት። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በናዝሬት በከብቶች በረት ሲወለድ ንጉሥ ሄሮድስን ጨምሮ እስራ

ኢላውያን፣ የአካባቢው መንግሥታትና ሕዝቦች (ግሪካውያን፣ ሮማውያ፣ ሶርያውያን) ወዘተ አላወቁም ነበር። ኢትዮጵያውያን ግን እግዚአብሔር ገና ከመወለዱ በፊት የትና መቼ እንደሚወለድ ገልጸላቸው፣ የሚመራቸው ኮከብ (ቅዱስ ገብርኤል) ሰጥቶአቸው፣ በንጉሣቸው ባዜን ወንድም (ሐውባዜን) መሪነት ወርቅ፣ ዕጣንና ከርቤ በመያዝ በቤተ ልሔም በመገኘት እጅ መንሻ አቅርበዋል፤ (ማቴ. 2፥11) በዚህም ከጌታችንና ከእናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም በረከትን አግኝተዋል፤ ከመላእክትና ከእረኞች ጋር በአንድነት እግዚአብሔርን በዜማ አመስግነዋል።

ዳግማዊ ታምሪን የሆነው የንግሥት ሕንደኬ ገንደረባ ቦኮስ በ34 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም በሄደ ጊዜ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በሐዋርያው ፊልጶስ አስተማሪነት በጋዛ ተጠምቆ ክርስትና ለመቀበል ቻለ (ሐዋ. 8፥26-40)። በመሆኑም ጌታ በተወለደ ከ34 ዓመት በኋላ በገንደረባው አማካኝነት ኢትዮጵያ ከክርስትና ጋር ለመተዋወቅ ቻለች፤ ኢትዮውያውያን በብሉይ ዘመን የነበራቸው የጠበቀ የእግዚአብሔር እምነት ክርስትና በአጭር ጊዜ በብዙ አካባቢዎች እንዲስፋፋ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አድርጓል። በዓለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን ኢትዮጵያውያን ከንግሥተ ሳባ ጊዜ ጀምሮ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ከእስራኤላውያን ውጭ ብቸኛ ባለርስቶች መሆን መቻላቸው ከክርስቶስ ልደት በኋላም ግንባር ቀደም ተሰሚነት ያላቸው ሕዝቦች እንዲሆኑ አግዞአቸዋል። ከሁሉም በላይ ግን የኢትዮጵያውያን ዝና በዓለም አቀፍ ደረጃ ገኖ እንዲወጣ ያስቻለው ቅድስናቸው ነበር።

ለአብነት ያህል እስከ 1694 ዓ.ም ድረስ በኢየሩሳሌም በፋሲካ በዓል ይደረግ የነበረው የብርሃን ማውጣት ሥርዓት የሚመራው በኢትዮጵያዊ ካህን ነበር። በዚህ በጎልጎታ መቅደስ ውስጥ የሁሉም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮችና መሪዎች በሚገኙበት ልዩና ደማቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት የሃይማኖት ድርጅቶች ተወካዮች ማዕርጋዊ አሰላለፍ (ቅደም ተከተል) የሚከተለው መልክ ነበረው።



ይኸውም:-

1ኛ. ኢትዮጵያዊ ካህን (ራኢስ)
2ኛ. የሮም ፓትርያርክ (በትሪክ)
3ኛ. የአርመን ራኢስ
4ኛ. የኩርጅ ራኢስ
5ኛ. የሶርያ ራኢስ
6ኛ. የግብፅ ራኢስ።

በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት ሁሉም ልብሰ ተክህኖአቸውን ለብሰው ቅዳሜ ምሽት (ቅዳሜ ሹር ዕለት) ጎልጎታ በሚገኘውና በወቅቱ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ ይዞታ በነበረው የጌታ መቃብር ይሰባሰባሉ። ሥነ ሥርዓቱን የሚመራው ኢትዮጵያዊ ካህን ለዚሁ ዓመታዊ በዓል ሲባል በየዓመቱ በንጉሡ ትእዛዝ ከኢትዮጵያ ይመጣ ነበር። አለባበሱም ከሁሉም በተለይ ነጭ ልብስ ነበር የሚለብሰው።

የብርሃን ማውጣቱ ሥነ ሥርዓት ሲጀመር ይህ ነጭ ልብስ የለበሰው ኢትዮጵያዊ ካህን ዘይት የመላበት ያልተቃጠለ ፈትል ያለበት የብርጭቆ ቀንዲል በእጁ ይዞ ወደ ውስጥ ይገባል። እንደገባም ደጃፉን ይዘጋል። የሮም ፓትርያርክን ጨምሮ ሌሎች ከተለያዩ ሀገራት የመጡ የሃይማኖት መሪዎች በየእጃቸው ያልተቀጣጠለ ጧፍ ይዘው ከውጭ ቆመው ይጠብቁታል።

ኢትዮጵያዊ ካህን ጸሎቱን እንደጨረሰ የያዘው ጧፍ ያለምንም ሰው ሠራሽ እሳት በእግዚአብሔር ኃይል በራሱ ይበራል። በዚህን ጊዜ ከውጭ ሆነው የሚጠባበቁ ገብተው እንዲሳለሙና ጧፎቻቸውን ማብራት ይችሉ ዘንድ ከውስጥ ሆኖ የመቃብሩን ደጅ ይመታል። ሲከፈትለት የሮም ፓትርያርክና የቀሩት ሙጥራኖች (ጳጳሳት) በየእጃቸው የያዙትን ጧፍ ኢትዮጵያዊው ካህን ከያዘው ቀንዲል እያያያዙ ፈጥነው ከመቃብሩ ይወጣሉ።[6]

[6] ደስታ ተክለ ወልድ - ገበታዋሪያ የንባብ መማሪያ - 1928 ዓ.ም ገጽ 46-47

በኢየሩሳሌም ዛሬ ድረስ የብርሃን ማውጣት ሥርዓት የሚከናወን ቢሆንም ኢትዮጵያውያን በሮማውያን ግፊት ቦታውን ከለቀቁ በኋላ እግዚአብሔር በሮማውያንና በአርመን ራሲስ ብርሃን እንዲወጣ ፈቃዱ ባለመሆኑ ይመስላል መብራት የማብራቱ ሥርዓት የሚከናወነው ጧፉን በክብሪትና በመሳሰሉ ሰው ሠራሽ እሳት በማቀጣጠል ነው።

በወቅቱ የውጭ መንግሥታት ኢትዮጵያን «የዮሐንስ ቀሲስ ሀገር» እያሉ ነበር የሚጠርዋት። ይህም ምናልባት በወቅቱ የኢትዮጵያ ነገሥታት ካህናት ጭምር ስለነበሩ ሳይሆን አይቀርም በማለት የታሪክ ጸሐፊዎች ግምታቸውን ይሰነዝራሉ። በእርግጥም ከቀደሙት ኢትዮጵያውያ ነገሥታት መካከል የቅድስና ማዕርግ አግኝተው በስማቸው ገዳም የተገደመላቸው፣ ታቦት የተቀረጸላቸው በርካታ ናቸው። ከነገሥታቱ በተጨማሪ በሐዋርያዊ ተጋድሎአቸው፣ በክርስቶስ ወታደርነታቸው በርካታ ገቢረ ተአምራት በመፈጸም ወደ ብቃት ደረጃ የደረሱና አጽማቸው ባረፈበት ቦታ ገዳም (ደብር) የተሠራላቸው ቅዱሳንና ቅዱሳት ኢትዮጵያውያን ቊጥር ከ104 በላይ ነው።[7] (ይህ ቍጥር ተሰዓቱ ቅዱሳንና በተከታታይ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ጻድቃንና ሰማዕታትን አያካትትም፤)

## ብፅዕናና ጵጵስና በኢትዮጵያ

ቀደም ሲል ለማሳየት እንደተሞከረው በአገራችን ኢትዮጵያ ብፅዕና በሥራ መገለጽ ከጀመረ በሺሕ የሚቆጠሩ ዓመታት ተቆጥረዋል። በጽሑፍ ደረጃ ብፁዕ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት ቅዱስ ያሬድ ነው። ቅዱስ ያሬድ ድጓውን ሲጽፍ «ብፁዕ አንተ ዮሐንስ» ብሎ ነው የሚጀምረው።

ከዚህም በላይ ቅዱስ ያሬድ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ከሣቴ

[7] ዜና መዋዕል ዘብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ ሐምሌ 5 ቀን 1989 ዓ.ም (ገጽ. 27-31)



ብርሃንና ጻድቁ አባ ዮሐኒን ብፁዕ እያለ ይጠራቸዋል። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም ብፁዕ የሚለውን የክብር መጠሪያ በተለያዩ ጽሑፎቻቸው ማስፈራቸውን ሊቃውንት ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራሷ ልጆች ለሆኑ ጳጳሳት ብፁዕ በሚለው የክብር ስም[6] መጥራት የጀመረችው የራሷ ጳጳሳት መሾም ከጀመረች በኋላ ነው። ግብፅ ሀገር ድረስ በመሄድ ግንቦት 25 ቀን 1921 ዓ.ም በሊቀ ጳጳስ አቡነ ዮሐንስ አንብሮተ እድ የጵጵስና ማዕርግ ያገኙት የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት የሚከተሉት ነበሩ።

1. ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፡- የቀድሞ ስማቸው መምህር ኃይለማርያም
2. ብፁዕ አቡነ አብርሃም፡- የቀድሞ ስማቸው መምህር ደስታ
3. ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ፡- የቀድሞ ስማቸው መምህር ወልደኪዳን
4. ብፁዕ አቡነ ሚካኤል፡- የቀድሞ ስማቸው መምህር ኃይለሚካኤል

በጊዜው እነዚህ አባቶች እንዴትና በምን መስፈርት ለዚህ ከፍተኛ መንፈሳዊ መዓርግ ሊመረጡ እንደቻሉ የሚያሳይ ዝርዝር የጽሑፍ መረጃ ባላገኝም በዕድሜ አንጋፋ የሆኑ ሊቃነ ጳጳሳትን ጠይቄ እንደ ነገሩኝ ምርጫው የተካኼደው በንጉሣዊያን ቤተሰቦችና ባለሥልጣናት አማካኝነት ነበር። በወቅቱ የምርጫውን ሂደት በተመለከተ ሁለት አመራጭ ሐሳቦች ቀርበው ነበር።

የመጀመሪያው «ከታላላቅ ገዳማት ብቃት ካላቸው አባቶች መካከል ይመረጡ» የሚል ሲሆን ሐሳቡን ያቀረቡት ራስ ኃይሉ ነበሩ። በአማራጭነት የቀረበው ሁለተኛ ሐሳብ «ከገዳም የሚመጡ አባቶች በራሳቸው የሚተማመኑ፣ በእምነታቸው የጸኑ፣ ስህተትን ዓይተው የማያልፉ በመሆናቸው አያሠሩንም፤ በመሆኑም እዚሁ አዲስ አበባ በአጠገባችን ካሉትና በቅርበት ከምናውቃቸው በትምህርታቸውና በመንፈሳዊ እቀ

[6] ይህ የክብር ስም በሕግ ደረጃ ሥራ ላይ መዋል የጀመረው በ1945 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው የቅዱስ ሲኖዶስ ደንብ ነው።

ማቸው የተሻሉትን እንምረጥ›› የሚል ነበር። በመጨረሻ ሁለተኛው ሐሳብ ተቀባይነት አገኘ። በዚሁ መሠረት፡-

1. መምህር ደስታ፡- የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የንስሐ አባት፣
2. መምህር ኃ/ማርያም፡- የአልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን የንስሐ አባት፣
3. መምህር ወልደ ኪዳን፡- የራስ ካሣ የንስሐ አባት፣
4. መምህር ኃ/ሚካኤል፡- ለጊዜው ስማቸው ያልታወቁ የቤተ መንግሥት ሴት ወይዘሮ የንስሐ አባት፣ የነበሩ ተመርጠው ቀረቡ።

የምርጫው ሥርዓት በጊዜው ተሰሚነት በነበራቸው ሰዎች ተጽእኖ ሥር የወደቀ እንደነበር በቀላሉ መገንዘብ ቢቻልም ሂደቱ መንፈስ ቅዱስ ያልተለየው እንደነበረ የሚያሳዩ ሁኔታዎች አሉ። ለምሳሌ ያህል እነዚህ አባቶች ለጵጵስና ሢመት ወደ ግብፅ በሄዱበት ወቅት በግብፅ ሀገር ከብዙ ጊዜ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ዝናብ ዘንቧል። በዚህም ግብፃውያን እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች የሀገራችንን መሬት በመርገጣቸው በረከት አገኘን በማለት ተደንቀው ነበር።

በወቅቱ በሀገሪቱ የታተሙ ጋዜጦችም ‹‹ከኢትዮጵያ ከመጡ እንግዶች ከዐራቱ አንዱ ‹‹ዓይን ያለው›› ነው (ከመካከላቸው ቅዱስ ሰው አለ) በማለት ጽፈዋል። ግብፃውያን የዝናቡን መዝነብ ካዩና ዜናውን ከጋዜጦች ካነበቡ በኋላ ኢትዮጵያውያኑን በዓይናቸው ለማየት ስለፈለጉ የጵጵስናው ሢመተ በዓል በተከናወነበት ዕለት ዐውደ ምሕረቱ (አደባባይ) በምእመናን ተጨናንቆ ነበር። በመጨረሻም ሊቀ ጳጳስ አቡነ ዮሐንስ ዐራቱን አባቶች ቅብዐ ሜሮን ከቀቡዋቸው በኋላ የቁድሞ ማዕርግ ቆባቸውን ከነመጠምጠሚያው በጠረጴዛ ላይ አኑረው የጵጵስና ማዕርግ ቆብ በራሳቸው ላይ ሲደፉላቸው በቤተ ክርስቲያኑ የተገኘው ሕዝብ ለበረከት እያለ በጠረጴዛው ላይ ተቀምጦ የነበረውን ቆብና መጠምጠሚያ በመቀስና በሰንጢ እየቆረጠ ተከፋፈለው።[7]

[7] ተክለ ብርሃን ዜና፦ ተክለተ ብርሃን ሐምሌ 22 ቀን 1933 ዓ.ም ገጽ 9



የእነዚህን አባቶች ብፅዕና የሚያሳይ ሌላም ማስረጃ እነሆ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ የተካኼደው እነዚህ ብፁዓን አባቶች ተሹመው በየሀገረ ስብከታቸው በተሰማሩ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ነበር። ከላይ ስማቸው ከተጠቀሰው ብፁዓን አባቶች መካከል አቡነ አብርሃምና አቡነ ይስሐቅ ለጊዜያዊ ጥቅምና ዓለማዊ ሹመት ሲሉ የጴማስን አርአያነት በመከተል፣ እምነታቸውን በማ..ደል ከጠላት ጎን ሲሰለፉ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስና ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ‹‹ምእመናኖቻችንን ለነጣቂ ተኩላ ሰጥተን አንሄድም›› በማለት ...ራቸው ነፃነትና ለሃይማኖታቸው ደማቸውን ለማፍሰስ ከጠላት ጋር ይፋለሙ ከነበሩ አርበኞች ጎን በመሰለፍ፣ ሕዝቡን በማጽናናት ለፋሽስት እንዳይገዛ በማስተማር፣ ‹‹ለወራሪ ጠላት የተገዛ ᐟርጉም ይሁን›› እያሉ በማውገዝ በጠላት ጥይት ተደብድበው እንደ አባቶቻቸው ሐዋርያት በአደባባይ የጽድቅ መሥዋዕትነት ተቀበሉ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እስከ አሁን በድምሩ አንድ መቶ አንድ (101)[8] ጳጳሳትንና አምስት ፓትርያርኮችን ሾማለች። ከእነዚህ መካከል ብዙዎቹ እንደነብፁዕ አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል በአቋማቸው፣ በአኗኗራቸው የሐዋርያትን መንገድ የተከተሉ ናቸው። እዚህ ላይ ብፁዕ አቡነ ታድዮስን (ዳግማዊ አትናቴዎስ ዘቂሳርያ) ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል። በ1953 ዓ.ም በእነ መንግሥቱ ነዋይ አማካኝነት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተደርጎ እንደነበር ይታ... በወቅቱ ታድያ በሁኔታው ያዘኑት ብፁዕ አቡነ ታድዮስ ‹‹ይህ የሆነው እኛ በሠራነው ኀጢአት ነው›› በማለት በምናኔ ደብረ ሊባኖስ ገቡ።

ደብረ ሊባኖስ ለተወሰነ ጊዜ ከቆዩ በኋላ ለበለጠ መንፈሳዊ ተጋድሎ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ተነሡ። ያኔ ወርሃዊ ደመወዛቸው ብር 500 (አምስት መቶ ብር) ነበር። ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ

[8] ዝክረ አበው (መጽሔት) 1996 ዓ.ም ገጽ 6

ሲነሡ ደመወዝዎ ወደዛ ይዛወርልዎ ሲባሉ ‹‹እኔ የምሄደው ለምንና ነው ደመወዝ ምን ያደርግልኛል›› በማለት እምቢ አሉ፡፡

ይልቁንም ከዛ በፊት ያጠራቀሙትንና በባንክ ቤት የነበረው ገንዘባቸውን ተወልደው ባደጉበት በየጁ ውስጥ ለምትገኘው ገነተ ልዑል ማርያም አውርሰው ሄዱ፡፡ እነሆ ገነተ ልዑል ማርያም እስከ አሁን ድረስ እንደቋሚ በጀት አድርጋ የምትተዳደረው ከእኒህ ብፁዕ አባት ባገኘችው ገንዘብ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያንዋ የምትተዳደረውም ዋናውን ሳትነካ ከወለዱ የሚገኘውን ትርፍ ገንዘብ በመጠቀም ብቻ ነው፡፡

ብፁዕ አቡነ ታድዮስ እንደሳሙኤል ከልጅነታቸው ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንዲሆኑ የተመረጡ ነበሩ፡፡ ብፁዕ አቡነ ታድዮስ ከሙስሊም ቤተሰብ የተገኙ ቢሆንም በልጅነታቸው ወቅት (ክርስትና ሳይነሱ) ጓደኞቻቸው መስጊድ እየሠሩ ሲጫወቱ እርሳቸው ቤተ ክር ስቲያን ይሠሩ ነበር፡፡ በየጊዜውም ርግብ እየመጣች ላያቸው ላይ ታርፍባቸው እንደነበር በቅርበት የሚያወቁዋቸው አበው መስክ ረውላቸዋል፡፡

ብፁዕ አቡነ ታድዮስ በጵጵስና ጊዜያቸው በብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ተወክለው ሰዎችን ያስምሉ በነበረበት ጊዜም በእጃቸው በርካታ ተአምራት መፈጸማቸው ይነገራል፡፡ ለምሳሌ መስማት ከተሳናት የወለደ አንድ መነኮሴ ተከሶ ቀርቦ በሳቸው ፊት ስለካደ በጥቂት ቀናት ውስጥ ሰውነቱ አባብጦ በመፈንዳት ሞቷል፡፡ በተመሳሳይ ታመውና በድንገት የተቀሰፉም ስለነበሩ እርሳቸው ፊት ቀርቦ የሚዋሽ አልነበረም ይባላል፡፡

በምናኔ ወደ ኢየሩሳሌም ከሄዱ በኋላም የዚህ ዓለም ነገር በቃኝ ብለው በባዶ እግራቸው በፍልስጥኤም በረሓ በመንዝ ሆነ ብለው ሰውነታቸውን በበረሓ ጊንጥ በማስነደፍና በመጉዳት ለኀልፈት መብቃታቸው ይታወቃል፡፡



በቅርቡ በኢየሩሳሌም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ብፁዕ አቡነ አብሳዲም ታሪካቸው ተመሳሳይ ነው፡፡ ብፁዕ አቡነ አብሳዲ የዐረብኛ ቋንቋ ችሎታቸውን በመጠቀምና በርካታ ሰነዶችን በማደራጀት ዴር ሡልጣንን ጨምሮ በኢየሩሳሌም ይገኙ የነበሩና በሌሎች አካላት ተወስደው የነበሩ በርካታ መካነ ቅዱሳት ለቤተ ክርስቲያናቸው ያስ መለሱ ቢሆንም እሳቸው ያርፉባት የነበረችው ክፍል ግን በጣም ጠባብ ከመሆንዋ የተነሣ አንድ ታጣፊ አልጋ እንኳን በወጉ የማታዘረጋ ነበረች፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን አቡነ ጴጥሮስ፣ አቡነ ሚካኤል፣ አቡነ ታድዮስና አቡነ አብሳዲ የመሳሰሉ ብፁዓን አባቶችን የመውለዷ ያህል የአቡነ አብርሃምና አቡነ ይስሐቅን መስመር ተከትለው መንፈሳዊ ሹመታቸውን በዓለማዊው ክብር የለውጡ አንዳንድ ‹‹ብፁዓን›› እንደነበሩና አሁንም እንዳሉ ፀሐይ የሞቀው ሕዝብ ያወቀው እውነት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለጵጵስና ሲመት እንደመስፈርት አድርጋ ስትጠቀምባቸው የቆዩ መለኪያዎች ምንጫቸው በዋናነት ሐዋርያት ያስቀመጡዋቸው መለኪያዎችና መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው የወጡ ናቸው (1ጢሞ. 3፥1-7፣ ቲቶ.1፥7-9)፡፡

### ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

- ኤጲስ ቆጶስ ከምግብና ከመጠጥ ለቁመተ ሥጋ ያህል ይውሰድ፣ ያስተማሩትን ለማስተማር እንዲችል፣ ቸልም እንዳይል አብዝቶ እያወጣጣ፣ ዘዋሪ ሰውንም የሚበድል አይሁን፡፡ የሳመ የጣመ አይቅመስ፣ ዘወትር ያስተምር፡፡ የእግዚአብሔርንም መጻ ሕፍት ይመልከት፣ መጻሕፍትን አስረድቶ ይተረጉም ዘንድ ክፍል ክፍሉን በጥን ቃቁ ለይቶ ይወቀው፡፡ ወንጌልን ኦሪትንና ነቢያትን ይተርጉም፡፡ ጌታችንም ‹‹መጻሕፍትን ተመልከቱ እነርሱ ስለእኔ ይመሰክራሉና›› አለ (ዮሐ. 5፥39፣ ፈ.መ. 5፥11)፡፡
- አምላክ አዝዞ ያጻፋቸውን፣ የአምላክን ነገር የሚናገሩትን ብሉያትን ሐዲሳትን

ያልተማረ፣ ደልቁንም በራቱን ወንጌል ያልተረገመ አይሾም (ባስ. 89፥47)[9]::

- ኤጲስ ቆጶስ ከምግብና ከልብስ የሚበቃውን ያህል የሚወስድ ይሁን፣ ለሚያስፈልገው ዋጋው ይገባዋልና። ልብሱን አያሳምር፣ ሥጋውን ለመሸፈን የሚበቃውን ያህል ይውሰድ እንጂ፣ ቤሳ ጌጥ የሚያስፈልግ አይደለም (ፍ.መ. 5፥127)::
- ሐር ወይም ቀጭን ልብስ የሚለብስ ወይም በአገሩ ነዳያን ተርበውና ታርዘው ሳሉ ልዩ ልዩ ጣዕም ባለው ምግብ ማዕድን የሚያስጌጥ ኤጲስ ቆጶስ አይደለም (ፍ.መ. 5፥142)::
- ሲሾም በሚሾምባቸው ሕዝቦችና በሊቀ ጳጳሳቱም ፈቃድ ይሁን (ድስቅ 36)::
- ኤጲስ ቆጶስ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ በሕዝብ ምርጫ ይሾም (ፍ.መ. 5፥91)::
- ኤጲስ ቆጶሱ ከተሾሙ በኋላ በቤተ መቅደስ ውስጥ ዕሙድ ይሁን፣ በቤተ ክርስቲያን ይቀመጥ (ፍ.መ. 5፥112፣ 118)::
- ኤጲስ ቆጶስ ስራሱ ጥሪት (ሀብት ንብረት) አያብጅ፣ የሳመ የጣመ ስመቅመስ ታዘዙኝ ስማለትም አይድከም፣ ጊዜ ሳይወስኑ መገዛት ስእግዚአብሔር ብቻ ነውና (ፍ.መ.4፥77)::

ከዚህ በላይ ሊቃነ ጳጳሳትን በተመለከተ የቀረቡት ጥቅሶች በፍትሐ መንፈሳዊም ሆነ በሌሎች የሥርዓት መጻሕፍት ከሰፈሩት ተቆንጥረው የቀረቡ ቢሆንም ከዚህ ቀጥዬ ለማቀርባቸው ዝርዝር ሐተታዎች በቂ መንደርደሪያ ይሆናሉ ብዬ አምናለሁ። ቁም ነገሩ ቤተ ክርስቲያንዋ ከሐዋርያት የተረከበቻቸውንም ሆነ ራስዋ ያወጣቻቸውን ሕጎች ምን ያህል ተግባር ላይ ታውላቸዋለች ወይም እያዋለቻቸው ነው? የሚለው ነውና።

ቀደም ሲል ከጠቃቀስናቸው መስፈርቶች በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው የተለያዩ ደንቦችን እያወጣች ስትሠራ ቆይታለች። በቅዱስ ሲኖዶስ ደረጃ በደንብ (ሕግ) ደረጃ ወጥተው ሥራ ላይ ከዋሉት ደንቦች ዋና ዋናዎቹ በ1945፣ 1971፣ 1984፣ 1988ና 1991 ዓ.ም የወጡ ደንቦች ናቸው። እነዚህ

[9] ይህ መስፈርት ለካህናትና ዲያቆናት ሁሉ ያገለግላል።



ደንቦች በውስጣቸው ያካተቱዋቸው ዝርዝር ጉዳዮችን ትተን ‹‹ብፁዓን እነማን ናቸው?›› ከሚለው ርእስ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያላቸውን ማለትም፦

1. የኤጲስ ቆጶሳት አመራረጥ ሂደት
2. ለኤጲስ ቆጶስነት የሚያበቁ መስኪያዎች
3. የቅዱስ ሲኖዶስ ትርጓሜ
4. የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የግል ሀብትና ዜግነት ጉዳይ የሚሉትን እንመለከት።

## የኤጲስ ቆጶሳት (ሲቃነ ጳጳሳት) አመራረጥ ሥርዓት

በ1945 ዓ.ም በወጣው የቅዱስ ሲኖዶስ ደንብ[10] አምስተኛ አንቀጽ ‹‹ሀ›› ሥር ስለ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ምርጫን አስመልክቶ የሰፈረው እንዲህ ይላል፦

‹‹ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጳሳት ከመነኮሳት መካከል በየሀገረ ስብከቱ ምእመናን ከተመረጡ በኋላ ሥርዓተ ሢመታቸው እንደ ሕጉ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ይፈጸማል፣ ሹመታቸውም በመንግሥት ማስታወቂያ ይረጋገጣል።››

ይህ አሠራር የሐዋርያትን የምርጫ አሠራርና በፍትሐ መንፈሳዊ የሰፈረውን መስፈርት ከሞላ ጎደል የሚያሟላ ግልጽነትና የሕዝብ አሳታፊነት ያለው ነው። በወቅቱ ጳጳሳት የሚመረጡት በምእመናን ተሳትፎ ጭምር መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከተመረጡ በኋላ የሚመደቡት እንደ ሕጉ በተመረጡበት አካባቢ ነበር።

በዚህ ላይ ዝርዝር አስተያየት ከማቅረቤ በፊት በዚህ የጳጳሳት ምርጫ ዙርያ በተከታታይ የወጡ ሌሎች ደንቦች ምን እንደሚሉ እንይ።

[10] ደንቡ የወጣው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ከመሆናቸው በፊት ‹‹ብሊቀ ጳጳስ›› መዓርግ በነበሩበት ጊዜ ነው።

በ1971 ዓ.ም በወጣው ደንብ ምዕራፍ 4 ላይ የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ በሚለው ሥር ቍጥር 2 ላይ የሰፈረው እንዲህ ይላል፡፡

‹‹በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀናና መሠረት የኤጲስ ቆጶስ ምርጫ በድንግልና ከመነኮሱ ቀሞሳት መካከል ይሆናል፡፡››

<u>የ1984 ዓ.ም ደንብ፡-</u> ‹‹የኤጲስ ቆጶስ ምርጫ፡- በቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና ከሚሾምበት ሀገረ ስብከት ጥንታውያን ገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች፣ ከሚሾምበት ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ አባላት፣ በካህናትና በምእመናን ተወካዮች መራጭነት ይፈጸማል፡፡››[11]

<u>የ1988 ዓ.ም ደንብ፡-</u> ‹‹የኤጲስ ቆጶስ ምርጫ፡- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀናና መሠረት በሥርዓት ምንኵስና በድንግልና መንኵሰው በመነኮሱበት ገዳም ከሦስት ዓመታት ያላነሰ ጊዜ ያገለገሉና ለኤጲስ ቆጶስነት ምርጫ ብቁ ከሆኑት ቀሞሳት መካከል ነው፡፡[12]››

<u>የ1991 ዓ.ም ሕገ ቤተ ክርስቲያን፡-</u> የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ፡- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀናና መሠረት የኤጲስ ቆጶስ ምርጫ የሚፈጸመው፡-

1. ኤጲስ ቆጶስ እንዲሾም አስፈላጊ መሆኑ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሲታመንበትና ሲወሰን፣
2. በሥርዓተ ምንኵስና በድንግልና መንኵሰው ቤተ ክርስቲያንን ከሚያገለግሉና ለኤጲስ ቆጶስነት ብቁ ከሆኑት ቀሞሳት መካከል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ዕጩ ሆኖ ሲቀርብ፡፡[13]

የኤጲስ ቆጶስነትን የአመራረጥ ሥርዓት በተመለከተ በተለያዩ ዘመናት ከወጡት ሕግጋተ ቤተ ክርስቲያን መገንዘብ እንደሚቻለው ከ1984ቱ በስተቀር የተቀሩት የምእመናንና የካህናት ተሳትፎ የሰረዙ፣ የቤተ ክርስቲያን ቀኖናና ሥርዓት በሚል ድፍን ያለ ሐረግ የተሸፈኑ ናቸው፡፡ የ1984ቱ ቢሆንም ከተቀሩት ይሻላል ለማለት እንጂ የአበው ሐዋርያት ትእዛዝና የፍትሕ መንፈሳዊ ድንጋጌዎችን ሙሉ በሙሉ የሚያሟላ አይደለም፡፡

[11] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የ1984 ዓ.ም ሕገ ቤተ ክርስቲያን ምዕ. 4 ቍ. 4

[12] 1988 ዓ.ም ደንብ አንቀጽ 17 ‹‹ረ›› የዕድሜ መስፈርቶች ተከትሎ ‹‹በቅዱስ ፓትርያርኩና በቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በዕጩነት ተመርጠው ከቀረቡት ቀሞሳት መካከል ሰሣ የወጣለት ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ይሾማል›› ይላል፡፡

[13] 1991 ሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ 18 ቍ.1፣2



## ስለኤጲስ ቆጶስነት የሚያበቁ መስኪያዎች (መስፈርቶች)

በ1945 ከወጣው ደንብ በስተቀር ሌሎች ሕጎች ለኤጲስ ቆጶስነት የሚመረጥ አባት ሊያሟላቸው ይገባል ያልዋቸውን መስፈርቶች በዝርዝር አስቀምጠዋል፡፡ የመጀመሪያው ደንብ ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ያሰፈረው ነገር የለም፡፡ ምናልባትም ‹‹እንደ ሕጉ›› ብሎ የጠቀሰው ቤተ ክርስቲያን ፍትሕ መንፈሳዊውን እንደቋሚ ሕግዋ አድርጋ ትወስድ ስለነበር በዚህ ሕግ የተዘረዘሩት መስፈርቶች ማለቱ ሊሆን ይችላል፡፡

በተረፈ ከ1971-1991 ዓ.ም ባለው ጊዜ የወጡ ዐራቱ ሕግጋተ ቤተ ክርስቲያን እንደመስፈርት አድርገው ያስቀመጧቸው ከሞላ ጎደል ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ፣[14]
2. በሃይማኖት ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ፣*
3. በግብረ ገብነት የተመሰገነ ፣
4. በትምህርተ ሃይማኖት (በነገረ መለኮት) በቂ ችሎታ ያለውና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቆ ያወቀ፣
5. ከምንኵስና በኋላ በገዳም ቢያንስ ለሦስት ዓመት ያገለገለ፣*
6. ሙሉ አካል ያለው፣ ጤንነቱ የተሟላ
7. የአስተዳደር ልምድና ችሎታ ያለው፣

ዕድሜን በተመለከተ የወጡ መስፈርቶች ግን ወጥነት የላቸውም፡፡ ፍትሕ መንፈሳዊ አንድ ሰው ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ለመሾም ዕድሜው ቢያንስ 50 መሆን አለበት ቢልም ከላይ ከጠቀስናቸው ሕጎች አንዳቸውም ይህንን አልተከተሉም፡፡ በመሆኑም በ1971 ዓ.ም የወጣው ደንብ ‹‹ዕድሜው ከ40 ያላነሰ ከ55 ያልበለጠ›› ሲል በ1984 ዓ.ም የወጣው ደግሞ

[14] 1988ና 1991 ዓ.ም በወጡ ሕጎች ላይ በተራ ቍ. 1 ከተጠቀሱት በተጨማሪ ‹‹ባይሆንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ ሆኖ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ጠንቅቆ ያወቀ›› የሚል ታክሎበታል፡፡

* በ1988 ዓ.ም የወጣው ደንብ በተራ ቍ. 2ና5 የተጠቀሱትን ግዴታዎች አላካተተም

የመነሻ ዕድሜ ክልሉን ብቻ በመወሰን ዕድሜው ከ40 ዓመት ያላነሰ በማለት ጣሪያውን አልፎታል። የ1988ቱ ሕገ ቤተ ክርስቲያን በአንጻሩ ዕድሜው ከ40-50 ዓመት ይሆናል ይላል። በ1991 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው ሕገ ቤተ ክርስቲያን በበኩሉ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ የሚመረጥ ዕድ ሜው ከ45-60 ዓመት የሆነው ነው በማለት ያስቀምጣል።

ዕድሜን በተመለከተ የወጡት ደንቦች የየራሻቸው የሆነ መስፈርት ይዘው የወጡበት ምክንያት ያልተብራራ (ጭራሹኑ ያልተጠቀሰ) ቢሆንም አንዳንድ ብፁዓን አባቶችን ጠይቄ እንደተረዳሁት የዕድሜው መስፈርት ውጥንት ያልያዘው በየጊዜው በሚደረጉ የብፁዓን አባቶች ምርጫ አንዳንድ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት እንዲሾሙላቸው የሚፈ ልጉዋቸውን ሰዎችን ላለማስቀረት ሲሉ በሚያወጡት ‹‹በልክ የተሰፋ›› መስኪያ ምክንያት ነው። ይህም የምርጫው ሂደት ከአድልዎ ያልጸዳ እንደነበር ጠቋሚ ምልክት ነው።

አድሎአዊነትና ግልጽነት የጎደለው አሠራር የታየበት ዕድሜን የተመ ለከተው መስፈርት አይደለም፣ ‹‹ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቆ ያውቀ፣ በነገረ መለኮት በቂ ችሎታ ያለው...›› የሚሉ የዕውቀት መስኪያ መስፈ ርቶችም ‹‹ሾላ በድፍን›› ዓይነት ይዘት ያላቸው በማያሻማ ሁኔታ ጥሬ ውንና ብስሉን ለመለየት የማያስችሉ ‹‹ተፈላጊ›› የሆኑ ሰዎችን ለማ ቀፍ ሲባል የቀረቡ ይመስላል።

አንዳንድ ሰዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ከትምህርት ብቃት አኳያ ሲመዘኑ ክፊሉ ብስል ክፊሉ ጥሬ፣ ክፊሉ የላመ፣ ክፊሉ የተሸረከተ አንዳንዶቹ ዐይናማዎች ሌሎቹ ተመሪዎች ሆነው የመገኘታቸው አንዱ ምክንያትም ይኸው ነው የሚሉትም ከዚሁ ተነስተው ሳይሆን አይቀርም።

## የቅዱስ ሲኖዶስ ትርጓሜ

በ1945 ዓ.ም ከወጣው ሕገ ቤተ ክርስቲያን በስተቀር የተቀሩት ደንቦች ለቅዱስ ሲኖዶስ የሰጡት ትርጉም በይዘት ተመሳሳይና አንድ ዓይነት ነው ማለት ይቻላል።



‹‹ሲኖዶስ ማለት ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለመወሰን የሚደረግ የጳጳሳት ጉባኤ ነው።›› (የ1971ና 1984 ዓ.ም ደንቦች)

‹‹ሲኖዶስ ማለት ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለመወሰን የሚደረግ የሲቃነ የጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ጉባኤ ነው።›› (1988 ዓ.ም ደንብ)

‹‹ቅዱስ ሲኖዶስ ማለት ፓትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት የሚያ ደርጉት ዓቢይ ጉባኤ ነው።›› (የ1991 ዓ.ም ሕገ ቤተ ክርስቲያን)

በ1945 ዓ.ም የወጣው ደንብ የሲኖዶስን ትርጉም ሲሰጥ ከላይ ከተጠ ቀሱት ትርጉሞች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም ይኸው ደንብ ከሐዋርያት ተያይዞ የመጣ አንድ ታላቅ ቁም ነገርን አካቷል፤ እንዲህ ይላል።

‹‹ቅዱስ ሲኖዶስ ማለት ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት የሚሰበሰብበት ጉባኤ ነው። .... አባላቶቹም ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ደግሞም ቅዱስ ሲኖዶስ የፈቀደላቸው በሃይማኖታቸውና በሊቅነታቸው የታወቁ ብቻ ናቸው።››

ከላይ ለማሳያ ከጠቃቀስናቸውና በተለያዩ ጊዜያት ከወጡ ሕግጋተ ቤተ ክርስቲያን መገንዘብ እንደሚቻለው ሐዋርያትና አበው ሊቃውንት ለቤተ ክርስቲያን እድገት ይበጃሉ ብለው የደነገጉዋቸው ደንቦች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸራረፉ፣ እየተቆራረሱ መምጣታቸውን ነው፤ ‹‹እያደሩ እንደ ጨረቃ ማነስ›› ይሏል ይህ ነው።

ይህ መጽሐፍ እስከተዘጋጀበት እስከ 2002 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በሥራ ላይ የነበረው የ1991 ዓ.ም ሕገ ቤተ ክርስቲያን በወጣበት ወቅት አንጋፋውን ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሚካኤልን ለማነጋገር ዕድል ገጥሞኝ ነበር፣ ብፁዕነታቸው በወቅቱ እንደገለጹልኝ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕገ ደንብ ጉድለት ማሳየት የጀመረው ከሁለተኛው ፓትርያርክ ከብፁዕ ወቅ ዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጊዜ ጀምሮ ነው። ለዚህ ዋና ምክንያቱ ደግሞ ቀደም ሲል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ወቅት ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመሰብሰብ በሳልና ሞያዊ ሐሳብ ይሰጡ የነበሩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ባለመካተታቸው የፈጠረው ክፍተት ነው። ብፁዕነታቸው ይህንን አስመልክተው እንዲህ ነበር ያሉት።

‹‹ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጊዜ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያናችንን ሕገ ደንብ ለማውጣትም ሆነ የወጡት ሕጎችን ለማስፈጸም ቅዱስ ሲኖዶስ ብቻውን በቂ አይደለም እያልኩ ስከራከር ቆይቻለሁ፤ ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር ምሁራን፣ በምእመናን ዘንድ ተደማጭነት ያላቸው የሕዝብ ተወካዮች፣ በአንድነት ሆነው ተከራክረው፣ ተወያይተው ጨምቀው የሚያወጡት ሐሳብ ነው መሆን ያለበት፡፡ በተረፈ ዐሥራ አምስትና ሃያ ጳጳሳት ብቻችን ሆነን እንዲህ ይሁን ብንል አስቸጋሪ ነው፤ የኛ ቅርሶች ምእመናን ናቸው፣ ስለዚህ ምእመናንን በፍቅር መያዝ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ምእመናኖቿን፣ ምእመናንም ቤተ ክርስቲያናቸውን ማቀፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡››[15]

በአጠቃላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሥር እየሰደዱ የመጡ ደካማ አሠራሮችና ከቤተ ክርስቲያን ሕይወት ጋር የማይጣጣሙ ሕጎች ዛሬ ጎልተው እየታዩ ላሉ የተዛቡ ሂደቶች እንዲከሰቱ መንስኤ ሆኑ፡፡ እስቲ በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያንዋ በተለይ ደግሞ በአንዳንድ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና በቅዱስ ሲኖዶስ እየተንጸባረቁ ያሉትን ደካማ ጎኖች ማስረጃ እያጣቀስን እንዳስሳቸው፡፡

## ስመንጋው ሁሉና ስራሳችሁ ተጠንቀቁ

(ሐዋ. 20፥28)

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ የማዳን ሥራውን የጀመረው ወንጌልን በማስተማርና ሕሙማንን በመፈወስ ነበር፡፡ ሐዋርያትን መርጦ ለሥራ ሲያስማራቸውም የሰጣቸው ትእዛዝ ‹‹ሂዱና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ›› (ማር. 16፥15) የሚል ነበር፡፡

ከሙታን ተነሥቶ ከማረጉ በፊት ለሐዋርያቱ ለሦስተኛ ጊዜ በተገለጠላቸው ወቅትም ‹‹ብፁዕ›› ብሎ ለሾመው ለጴጥሮስ፦ ‹‹ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?›› ሲል ሦስቴ ከጠየቀው በኋላ፦

[15] ፈለገ ጥበብ መጽሔት፦ ሚያዝያ - ሰኔ 1992 ዓ.ም ቁ.4 (ገጽ 23)



‹‹ከወደድከኝ ግልገሎቼን አሰማራ፣ ጠቦቶቼን ጠብቅ፣ በጎቼን አሰማራ›› (ዮሐ. 21፥15-17)

በማለት ነበር ታላቅ አደራ ያስረከበው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም በእስያ የነበሩ ደቀ መዛሙርቱን ለመጨረሻ ጊዜ በተሰናበታቸው ጊዜ፦

‹‹እሁንም በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ››(ሐዋ. 20፥28)፡፡

በማለት ያስተላለፈው መልእክት ብፁዓን አባቶች በጎቻቸውን ከነጣቂ ተኵላ የመጠበቅና በተገቢው መስክ የማሰማራት ግዴታ እንዳለባቸው በአጽንኦት አስገንዝቧል፡፡

ኢትዮጵያውያን መምህራን፣ ጻድቃን ሰማዕታትና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በደማቸውና በአጥንታቸው በማይነቃነቅ ዐለት ላይ እንድትመሠረት ያደረጉት ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ከራሳቸው ይልቅ በጎቻቸውን በመውደድ በሚገባ ጠብቀው በመያዛቸው፣ በጎቻቸውን ብቻ ሳይሆን ‹‹ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ›› (1ጴጥ. 5፥3) ‹‹በቃልና በኑሮ፣ በፍቅርም በእምነትም፣ በንጽሕናም ለሚያምኑት ምሳሌ ሁን›› (1ጢሞ. 4፥14፣ 11-12) በተባለው መሠረት ራሳቸውን ከዚህ ዓለም ጉድፍ ጠብቀው በንጽሕና መንገድ በመጓዛቸው ነው፡፡

ዛሬም ቢሆን በቍጥር ብዙ ባይሆኑም ለቀናት፣ ለሳምንታትና ለወራት፣ በመኪና፣ በበቅሎና በእግራቸው ጭምር ዳገት ቁልቁለት በበዛበት ቦታ እየተጓዙ ሐዋርያዊ ተልእኮአቸውን የሚወጡ፣ ምእመናንን እያጽናኑ፣ ገዳማትንና የገጠር አብያተ ክርስቲያናትን እያነጹ፣ የአብነት መምህራንንና ደቀ መዛሙርቶቻቸውን እየደገፉ፣ ልማትን እያስፋፉ በአጠቃላይ ለነገ የሚሆን ቋሚ ሥራ እየሠሩ ያሉ ብፁዓን አባቶች አሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነት የተቀደሰ ተግባር የሚፈጽሙ አባቶች በትምህርት የበሰሉ፣ ዕድሜአቸውን በሙሉ ከቀለም ጋር በመታገል የሳለፉ፣ ሌት

ተቀን ከቤተ መቅደስ የማይለዩ፣ ጸሎት ስንታቸው፣ እግዚአብሔር ምርኩዛቸው አድርገው የሚጓዙ፣ ‹‹እስመ ብዙኀን ጽውዓን ወኀዳጣን ኀሩያን = የተጠሩ ብዙዎች የተመረጡት ግን ጥቂቶች›› (ማቴ. 20፥16) እንደተባለ ለጽጽስና ከተጠሩ ብዙዎች መካከል መስፈርቱን አሟልተው የተገኙ ሐዋርያትን የመሰልዋቸው ናቸው።

በአንጻሩ ከበጎቻቸው ይልቅ ራሳቸውን የሚያስማሩ፣ ወደ ቤተ ክርስ ቲያን ከመሄድ ይልቅ እንደ ዴማስ ወደ ከተማ ኀራ ማለቱን የሚቀ ናቸው፣ ከቤተ መቅደስ ይልቅ በየድግስ ቤቱ መገኘቱን የሚያዘወትሩ ጥቂት ሊቃነ ጳጳሳትም አሉ። ዛሬ የሊቃነ ጳጳሳቱ ቊጥር ከዐርባ በላይ ሆኖ እያለ በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ምእመናን የትም እየተ በተኑና በአራዊት እየተበሉ (ሕዝ. 34፥3-10) የሚገኙበት ምክንያትም ሊቃነ ጳጳሳቱ ተቀዳሚ ተግባራቸው የሆነውን የስብከተ ወንጌል ተልእኮ ችላ በማለታቸው ነው። ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ ይህንን በተመለከተ ሐምሌ 5 ቀን 2001 ዓ.ም በታተመው የቅዱስ ፓትርያርኩ በዓለ ሢመት መጽሔት ያሰፈሩት መልእክት ይህንን እውነታ አጉልቶ ያሳያል። እንዲህ ይላል፦

‹‹ሐጺስ ቀጸስ ጠባቂ ነውና ደጠብቅ ተብሏል። እንደተባለው መንጋው ተጠብቋል ወይስ አልተጠበቀም? መንጋው አልተጠበቀም የሚለው መልስ እንደሚገባ ግልጽ ነው። ይህንም የሚያሳየው ያለፈው ዓመት የሕዝብ ቆጠራ ነው። መንጋው በትክክል ከተጠበቀ 7,000,000 (ሰባት ሚሊዮን) ያህል ሕዝበ ክርስቲያን ለምን ቀነሰ? ይህን ያህል መንጋ በመናፍቃን ተሠርቋል ወይም ወደ ሌላ ሃይማኖት ተወስዷል ማለት ነው።››[16]

ከላይ የሰፈረው ቁም ነገር የሚያሳየው ነገር ቢኖር ቅዱስ ሲኖዶስ ለስብከተ ወንጌል የሰጠው ትኩረት እየቀነሰ መምጣቱን ነው። ለአብነት ያህል በ1945 ዓ.ም የወጣው ሕገ ቤተ ክርስቲያን ለስበከተ

16 መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት፦ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በ17ኛ ዓመት የፓትርያርክነት በዐለ ሢመት መጽሔት (ገጽ. 100) 2001 ዓ.ም



ወንጌል ልዩ ትኩረት ከመስጠቱም በላይ ለዚህ ተግባር አፈጻጸም የሚረዱ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ዝርዝር መመሪያ ነበረው። ለአብነት ያህል ስብከተ ወንጌል መምሪያው፦

* ለስብከት የሚረዱ መጻሕፍትን የማተም፤
* በየትምህርት ቤቱ የሚያስተምሩ መምህራንን የመመልመል፤
* በግለሰቦችና በሌሎች አካላት የሚዘጋጁ መንፈሳዊ መጻሕፍት ከመታተማቸው በፊት የመመርመርና የመፍቀድ፤
* ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ምእመናንን የማስተማር፤
* መጻሕፍት ቤቶችንና ሙዚየሞችን የማቋቋም፤
* ወደተለያዩ የአገሪቱ ቋንቋዎች የሚተረጐሙትን መጻሕፍት ጥራትና ይዘት የመቆጣጠር፤

የመሳሰሉት ተግባራት የማስፈጸምና የመፈጸም ሥልጣንና ኃላፊነት ነበረው። ከዚህ በኋላ የወጡ ደንቦች ግን አንዳቸውም ቢሆኑ ስለ ስብከተ ወንጌል ሥራ ዝርዝር ያወሱበት ጊዜ የለም።

ሌላው አስገራሚ ጉዳይ በ1984 ዓ.ም በወጣው ሕገ ቤተ ክርስ ቲያን አንቀጽ 20 ሥር ከቅዱስ ሲኖዶስ በቀጥታ መመሪያ እየተቀበሉ የሚሠሩ ተብለው ከተዘረዘሩት ስድስት ድርጅቶች፣ የትምህርት ተቋ ማትና መምሪያዎች መካከል የስብከተ ወንጌል መምሪያ አለመጠቀሱ ነው። ለመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ ከስብከተ ወንጌል የሚበልጥ ምን ዓይነት ሥራ ቢኖረው ይሆን እንዲህ ያደረገው? ወይስ፦

‹‹ሕዝቤ የጠፉ በጎች ሆነዋል፤ እረኞቻቸው አሳቱአቸው፤ በተራሮች ላይ የተቅ በዘበዙ አደረጉአቸው፤ ከተራራ ወደ ተራራ አለፉ፤ በረታቸውንም ረሱ፤ ያገኙአቸው ሁሉ በሉአቸው (ኤር. 50፥6-7)።

የሚለው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ይሆን? ወይስ፦

‹‹ለእስራኤል ቤት ጉበኛ አድርጌሃለሁ፤ ስለዚህ የአፌን ቃል ስማ በቃሌም

ገምጻቸው። እኔ ኃጢአተኛውን፤ በእርግጥ ትሞታለህ ባልሁት ጊዜ አንተም ባትነግረው ነፍሱም እንድትድን ከክፉ መንገዱ ይመለስ ዘንድ በኃጢአተኛው ባትነገረው ያ ኃጢአተኛ በኃጢአቱ ይሞታል፤ ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ›› (ሕዝ. 3፥17-18)።

የሚለው መልእክት በቀጥታ እነርሱን የሚመለከት መሆኑን ልብ አላሉት ይሆን?

ዛሬ ቤተ ክርስቲያንዋ ማንም ግለሰብ እየተነሣ ያሻውን የሚናገርባት፣ በዐውደ ምሕረቷ የሚጨፍርባት፣ በስብከትና በመዝሙር ስም የግል ሀብቱን የሚያከማችባት፣ ሲያሻው ፖለቲካ የሚሰብክባት፣ ሲያሻው ንግድ የሚያካሂድባት በአጠቃላይ መንገደኛው ሁሉ ያሻው የሚፈጽምባት የሆነችው እረኞቿ በጎቻቸውን ሜዳ ላይ ጥለው በመሄዳቸው ነው። ይህ ሁሉ ድክመት እየተከሰተ ያለው የቤተ ክርስቲያንዋ ዓይን የሆኑ ሰባኪያነ ወንጌልና ወጣት የከፍተኛ መንፈሳዊ ተቋማት ምሩቃን እንደ ሁለተኛ ዜጋ እየታዩ በተቃራኒው ትኩረቱም፣ ደመወዙም፣ ሥልጣኑም ዕርፍ መያዝ ለማይችሉ ሠራተኞች በመሰጠቱ ነው።

ምነው እግዚአብሔር፦ ‹‹ወደ ሕዝቤ ማንን እልካለሁ?›› ብሎ በጠየቀ ጊዜ እንደ ኢሳይያስና ሳሙኤል ‹‹እነሆኝ እኔን ላክ›› የሚል ጠፋ? (ኢሳ. 6፥8፤1ሳሙ. 3፥4)

## ወደ ከተማ ውጭ እንውጣ (ዕብ. 13.13)

ሕዝብ የሚኖረው በከተማና በመንደር ነውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን በቤተ መቅደስ እየተገኘና ወደ ሕዝቡ ዘንድ እየሄደ ያስተምራቸው፣ ከደዌ ነፍስ ከደዌ ሥጋ ይፈውሳቸው ነበር።

ሌሊቱን የሚሳልፈው ግን ከከተማ በመውጣት በደብረ ዘይት ተራራ ነበር። መጽሐፍ፦

‹‹ዕለት ዕለትም በመቅደስ ያስተምር ነበር፤ ሌሊት ግን ደብረ ዘይት ወደምትባል ተራራ ወጥቶ ያድር ነበር›› እንዲል (ሉቃ. 21፥37-38፤ ዮሐ. 8፥1-2)።



ሲቀ ጳጳስ ‹‹በቤተ ክርስቲያንህ ተቀመጥ›› (ፍ.መ 5፥111) በማለት የታዘዘውም ሊቃነ ጳጳሳት የጌታንና የሐዋርያትን መንገድ ተከትለው መሄድ እንዳለባቸው ለማዘከር ነው። በመሠረቱ ተራራ፦ ‹‹የሥልጣን፣ የሹመት፣ የልዕልና፣ የቅድስና፣ የክብርና የኃይል ተምሳሌት ነው።›› ተራራ፦ ‹‹መከታ፣ ከለላ፣ ጥላ መጠጊያ›› ማለትም ይሆናል። በተጨመሪያ እግዚአብሔር፣በኋላም እመ ብርሃን ቅድስት ድንግል ማርያም በተራራ (አምባ) ተመስለው ተጠርተውበታል (ዘዳ. 3፥24፤ መዝ. 30፥3፤ 95፥1፤ ኢሳ. 26፥4)። የታቦርና የደብረ ዘይት ተራሮችም በመቅደስ (በቤተ ክርስቲያን) ይመሰላሉ።

በተቃራኒው ዓለማዊ ከተማ የባቢሎን ተምሳሌት ነው። እስፍ ሲልም ገሀነም በቆላ፣ በሸለቆ፣ በጥልቅ ጉድጓድ ይመሰላል፤ የተራራ ተቃራኒ ነውና (ኢሳ. 14፥15፤ መዝ. 63፥9፤ ክ.ፋ. 8፥25፤ ሄኖ. 5፥28፤ ዘዳ. 32፥22)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከማስተማር መልስ በደብረ ዘይት ተራራ (ቤተ መቅደስ) ያድር እንደነበር ሁሉ፣ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን ያፈሰሰልንም በቀራንዮ ተራራ ላይ መሆኑ ማስታወሱ ተገቢ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ፦

‹‹አሁንም ተግዳርቱን ተሸክመን፤ ወደ እርሱ ወደ ከተማ ውጭ እንውጣ›› (ዕብ.13፥13)

ሲል ምቾትና ተድላ ከበዛበት፣ ኃጢአት ከሚዘወተርበት ከተማ ወጥተን ወደ ተቀደሰው ተራራ (ቤተ ክርስቲያን) እንሂድ ማለቱ ነው።

አበው ሊቃነ ጳጳሳት እንደዛሬው ለሚኖሩበት ብለው ሳይሆን ሰዎች ናቸውና ሲደክማቸው ዐረፍ የሚሉበት፣ ምግብ የሚቀምሱበት፣ ምእመናንን ተቀብለው የሚባርኩበት፣ የሚያጽናኑበት፣ መጻሕፍትን የሚፈትሹበት ቤት (መንበረ ጵጵስና) በቤተ መቅደስ ጓሮ የሚሠሩበት ምስጢርም ይኸው ነው። ባለንበት ዘመን ግን አንዳንድ ‹‹ብፁዓን››

አባቶች ይህንን ሕግ ጥሰው ‹‹በባቢሎን›› መካከልና በነጋዴዎች ሰፈር መለስተኛ ቤተ መንግሥት የሚያክል ሕንጻ ሲሠሩ፣ ተራራውን ትተው ‹‹ወደየ ሽለቆው›› ሲገቡ ይታያሉ፡፡

እነዚህ ‹‹ብፁዓን›› አባቶች ዓለምን ወደው የጀመሩትን የተራራ መን ገድ መውጣት አቅቷቸው ቊልቊል ወደ ከተማ የተመለሱ (2ጢሞ. 4፥10) ከጌታ የተቀበሉትን የወንጌል ዕርፍ ይዘው ወደ ፊት ማረስ ሲገባቸው ወደ ኋላቸው የተንሸራተቱ፣ (ሉቃ. 9፥6) የጣፈጠ ነገር ለመብላት ሲሉ በመንገድ የጠፉ፣ (ሲኢ. 4፥5) ‹‹ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነው፣ ስለመንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው›› (ሮሜ. 8፥6) የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ‹‹ሥጋዬ ከሞተ ነፍሴ ሠርዶ አይብ ቀልባት›› በሚል ዓለማዊ ብሂል ለውጠው በመንፈስ እያነሱ በሥጋ እየዘፉ የመጡ፣ ወደ ባቢሎን ለመሄድ የመልስ ጉዞ የጀመሩ ናቸው (ተ.ባ 5፥31፣ ተ.ኤ.11፥31)፡፡

እነዚህ ገና በጥዋቱ ለዚህ ከፍተኛ ሐዋርያዊ ኃላፊነት ሲታጩ አስቀድመው እንደ ሙሴና ዳዊት ‹‹እኔ ማን ነኝ?›› (ዘጸ. 3፥12፣ 1ሳሙ. 18፥18) ብለው በመጠየቅ ውስጣቸውን መፈተሽ ሲገባቸው፣ ከተሾሙ በኋላም ‹‹ሰዎች ማን ይሉኛል?›› (ሉቃ. 9፥18፣ ማቴ. 16፥13፣ ማር. 8፥27) በማለት ሌላውን ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት ራሳቸውን መስበክ ረስተው፣ በራሳቸው ዓይን የተጋደመውን ምሰሶ ሳያወጡ በሌላው ዓይን ያለውን ጉድፍ አግዝፈው ለማሳየት የሚጥሩ ‹‹አላዋቂ ተራች ለራሱ አመልካች›› ዓይነቶች ናቸው፡፡

ጳጳሳት የረገጡት ቦታ (ዐፈር) እንደ እምነት ሆኖ እንዳላገለገለ ሁሉ ዛሬ ዛሬ ሊቃነ ጳጳሳት በምእመናን እየተከሰሱ ዓለማዊ ፍርድ ቤት የሚቀርቡበት፣ ‹‹ከአካባቢያችን ለቀው ይውጡልን›› የሚል ተቃውሞ የሚሰማበት ጊዜም ተደርሷል፡፡

በእርግጥ የቤተ ክርስቲያናችን ጠላቶች የጠንካራ አባቶችን ስም ለማጥፋትና ቤተ ክርስቲያናችንን ለማዳከም ከሚል ስውር ዓላማቸው



በመነሣት በብፁዓን አባቶች መሠረተ ቢስ ክስ የሚያሰሙ እንዳሉ እውነት ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ የጠላት እንቅስቃሴ ዛሬ ቀርቶ በሐዋርያት ጊዜም የነበረ ነውና አያስደንቅም፡፡

ይሁን እንጂ አንዳንድ ‹‹ብፁዓን›› አባቶች ምእመናንን አስተምሮ ለማ ሳመን የሚያስችል የዕውቀት ብቃት ካለመያዛቸው የተነሣ ምእመናን በወንጌል ጥም በሚቃጠሉበት ጊዜ ከተቆርቋሪነትና ክርስቲያናዊ ስሜት በመነሣት በብፁዓን አባቶች ላይ የሚያነሱአቸው ቅሬታዎች እንዳሉም መታወቅ አለበት፡፡ ጥንትከ በአንድ ሀገረ ስብከት ከእምነትና አስተዳደር በተያያዘ የሚነሱ ችግሮችን የሚፈታው ሊቀ ጳጳሱ ነበር (የሐ. 15፥22)፡፡ አሁን አሁን ግን ሊቃነ ጳጳሳቱ አቅም ስለሚያንሳቸው ከማእከል ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እየተላኩ ነው ሁኔታዎችን የሚያረጋጉትና የሚያጣሩት፡፡

ከሁሉ ከሁሉ በላይ ግን ሊቃነ ጳጳሳቱ በዓለማውያን እየተከሰሱ ‹‹ስማቸው የሚጠፋውና›› በዓለማዊ ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡት ከመጀ መሪያው ራሳቸው ከቤተ መቅደሳቸው እየወጡ ከተማ ስለሚገቡና ‹‹ለሁለት ጌታ መታዘዝ አይቻልም›› የሚለውን ረስተው እንደ እግ ራቸው በቤተ መቅደስ ሌላውን በከተማ ለማቆም በመሞከራቸው ነው፡፡ ንብ ከቆፎውና ከሠራዊቱ ከተለየ እንደ ዝንብ ተልከስካሽ ሆኖ መቅ ረቱ የግድ ነውና፡፡

ሊቃነ ጳጳሳቱ ግን እየተከሰሱ ያሉት በሌሎች አካላትና ምእመናን ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳቸውም ጭምር ነው፡፡ የዚህ ምንጭ ደግሞ በዋናነት ቅዱስ ጳውሎስ፡-

‹‹ቅናትና ክርክር ስለሚገባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን?›› (1ቆር. 3፥3) እንዳለው ‹‹የተራራው›› ሥራቸውን ትተው በሥልጣንና በገንዘብ ምኞት የፈተና ወጥመድ ስለወደቁ ነው (1ጢሞ. 5፥9-10)፡፡

## ‹‹የመጨረሻው አንቀጽ››

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ‹‹የተለየ አንቀጽ›› በ1991 ዓ.ም በወጣው ሕገ ቤተ ክርስቲያን ሰፍሯል። በዚህ የመጨረሻው ዘመን ምልክት በሆነው የመጨረሻ አንቀጽ 45 ‹‹ስለቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ሀብትና ንብረት›› በሚል ርእስ ሥር ተራ ቍጥር አንድ ላይ እንዲህ የሚል ይነበባል።

1. አንድ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ የግል የሆነ ገንዘብ ቢኖረው ይረዳቸው ለነበሩ ዕጓለ ማውታና ችግረኞች ይሰጣል (አብጥሊስ 39)።

እዚህ ላይ ቤተ ክርስቲያንዋ ከ1945 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ባወጣቻቸው ሕጎች ያልነበረ ይህ አዲስ ደንብ በዚህ ጊዜ ማውጣት ለምን አስፈለገ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው። መልሱ ‹‹ሊቃነ ጳጳሳት የግል ሀብትና ንብረት ማፍራት በመጀመራቸው ነው›› የሚል ይሆናል፣ እሳት በሌለበት ጭስ አይጨስምና። ሲኖዶሱ ከላይ የተጠቀሰውን ደንብ ሕጋዊ ለማድረግ የተጠቀመበት ኢጋኘ መረጃ አብጥሊስ 39ን ነው።

ለመሆኑ አብጥሊስ ምንድነው? አብጥሊስ በዘመነ ሐዋርያት አበው ጊዜ የተጻፈ ስለ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናትና ምእመናን ኃላፊነት የሚናገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሥርዓተ መጻሕፍት አንዱ አድርጋ የምትቀበለው መጽሐፍ ነው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ መነሣት ያለበት ሁለተኛው ጥያቄ በእርግጥ አብጥሊስ የግል ሀብትና ንብረት የሚፈቅደው ለማን? መቼና ምን ሲሆን ነው? የሚለው ነው። እስቲ ይህንን በተመለከተ በዐበይት ሕግጋት በተለይ ስለ ርስት በሚያወራው አንቀጽ 42 ሥር ከሰፈሩት ቁም ነገሮች አንድ ሦስቱን እንመልከት፦



ቍ. 1381፦* 11ኛ ምዕራፍ ስለ ኤጲስ ቆጶሳትና ስለመነኮሳት አወራረስ ይናገራል። ረስጠጅ[17] 39 የኤጲስ ቆጶሱ ገንዘብ የታወቀ ይሁን። የቤተ ክርስቲያን የታወቀ ይሁን። የወደደውን ሊያደርግበት ለእርሱ በሆነው ላይ ሥልጣን ይኖረው ዘንድ ለወደደው ያወርሰው ዘንድ በቤተ ክርስቲያኑም ገንዘብ ምክንያት ገንዘቡ እንዳ ይጠፋበት።

ቍ. 1382፦ ለኤጲስ ቆጶሱ ዘመዶችና ልጆች ቢኖሩት የሚገባ ሥራ መሥራት በእግዚአብሔር ፊት ይህ ነው። ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ እንዳችም እንዳይጠፋ፣ ይበላውም ዘንድ ለወደደው እንዲሰጠው፣ ኤጲስ ቆጶሱንም በገንዘቡ እንዳ ይበድሉት፣ ቤተሰቦቹና ዘመዶቹ በቤተ ክርስቲያን ገንዘብ በማመካኘት ለእርሱ በሆነው ላይ እንዳይከራከሩ ይህም ከሞተ በኋላ ኃፍረትን፣ ውርደትን፣ ነቀፋን፣ ክፉ ስም አጠራርን፣ የሚያመጣ እንዳይሆን፣ (ጠስ.31) ዘመዶቹም በችጋር ላይ እንዳይወድቁና እርሱን እንዳይረግሙት፣

ቍ. 1383፦ (ጠስ 24) ኤጲስ ቆጶስ፣ ኤጲስ ቆጶስነት ከመሾሙ አስቀድሞ ያጠራቀመውን ገንዘብ ያስተዳድርበትና ያዝዝበት ዘንድ ለወደደው ሊሰጥ ይገባዋል። ከኤጲስ ቆጶስነቱ በኋላ ያጠራቀመው ገንዘብ ግን ለቤተ ክርስቲያን ይሁን። ከእርሱ በምንም ያዝዝ ዘንድ ለእርሱ ትእዛዝ አይገባውም።

ወደ ዝርዝር ጉዳዩ ከማለፋችን በፊት ልንገነዘበው የሚገባ ነገር ቢኖር አብጥሊስ ተጻፈ የሚባለው በዘመነ ሐዋርያት ጊዜ መሆኑን ነው። በወቅቱ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ሰፍሮ እንደምናገኘው ኤጲስ ቆጶስ ማለት ባለ አንድ ሚስትና የልጆች አባት ካህን ማለት ነው (1ጢሞ. 3፥1-2)። በወቅቱ የውርስ ጉዳይ የተነሣበት ዋናው ምክንያት ይኸው ነው።

ከዚህ ጋር አብሮ መወሳት ያለበት ተጨማሪ ቁምነገር አለ። በወቅቱ (የአብጥሊስ ሕግ በወጣበት ጊዜ) በርካታ አሕዛብ ካገቡና ትዳር ይዘው ልጆችና ንብረት ካፈሩ በኋላ ከመካከላቸው በሐዋርያት ትምህርት አምነው፣ ተጠምቀውና ክርስትና ተቀብለው በተራቸው ለማዕትነት ጭምር የከፈሉ በርካታዎች ነበሩ። ከዚህ አልፈው ተርፈውም እንደ

[17] ረስጠጅ አብጥሊስ ለማለት ነው

እነ አትናቴዎስ ዘቁሳርያ እስከ ጵጵስና ማዕርግ የደረሱ ነበሩ። በመሆኑም ምንም እንኳን ከተጠመቁ በኋላ ያለው ሕይወታቸው እግዚአብሔር አዲስ እንደተወለደ ሕፃን ንጹሕ የሚያደርግላቸው፣ እነርሱም እንደ ድንግል የሚቆጥራቸው ቢሆንም ከዛ በፊት በዓለም እያሉ ያፈሩትን ንብረት ለመከፋፈል ሲሉ ልጆቻቸውና ቤተሰቦቻቸው በሚያነሱት የይገባኛል ክርክር የባለንብረቱም ሆነ የቤተ ክርስቲያን ስም አለአግባብ እንዳይነሣ ታስቦ የወጣ የውርስ ሕግ መሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባል። በሌላ አገላለጽ አብጥሊስ ጳጳሳት ሕጋውያን ይሁኑ ነው የሚለው።

በአንጻሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶሳት ገና ከመጀመሪያው በድንግልና ሕግ ጸንተው፣ ከዓለም ተለይተው ወደ ገዳም በመግባት አባቱ እግዚአብሔር እናቱ ቤተ ክርስቲያን፣ ሕይወቱ ለእግዚአብሔር፣ ንብረቱ ለገዳም ብለው፣ ንብረት ቢኖራቸው ለገዳም አስረክበው፣ አባት እናታቸውን፣ እኅት ወንድማቸውን ትተው እግዚአብሔርን ብቻ ለማገልገል የወሰኑ ናቸው። ጉዳዩ እንዲህ ባይሆንማ ኖሮ ቀደም ሲል ሊቃነ ጳጳሳት ሊያሟሉአቸው የሚገቡ መስፈርቶች በሚል በሕግ ተረቀውና ጸድቀው ሥራ ላይ እንዲውሉ ባልተደረገ ነበር።

ስለሆነም በ1991 ዓ.ም በአንቀጽ 45 ተራ.ቍ. 1 ላይ የሰፈረው ሕግ ሥራ ላይ እንዲውል መፍቀድ በየትኛውም መስፈርት ተቀባይነት ያለው አይደለም። በአጭሩ ይህ ደንብ በአንድ በተፈጸመ ድርጊት ላይ ያልነበረ፣ ያላየና የልሰማ ሰውን ምስክር አድርጎ ከማቅረብ ያልተለየ ነው፤ ወይም ደግሞ ተልባን በመዝራት ላይ የነበረ መስማት የተሳነው ገበሬን አለመስማቱን ያላወቀ መንገደኛ በአጠገቡ ሲያልፍ ‹‹እንደምን ዋልክ?›› ሲለው ‹‹ምን እያደረግክ ነው?›› ያለው መስሎት ‹‹ተልባ እየዘራሁኝ ነው›› ብሎ እንደመለሰ ዓይነት መሆኑ ነው። በጥቅሉ ‹‹ሀብትና ንብረት›› የሚለው ሐረግ በራሱ መወሳትና መነሳት የሌለበት ነው። መነኵሴ በሕይወት እያለ ሙቻለሁ ብሎ ተገንዞ፣ ተገንዞ ተገኝኮሩ የወጣለት ሰው ነውና።



የአዲሱ ሕግ ችግር በዚህ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በተግባር እንደታየው የተሳሳተም ቢሆን የወጣው ሕግ በተግባር ላይ ሲውል አይታይም። ለምሳሌ ያህል ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በአንቀጽ 45 ቍ.1 ላይ የሰፈረው ‹‹አንድ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ የግል የሆነ ገንዘብ ቢኖረው ይረዳቸው ለነበሩ ዕጓለ ማውታና ችግረኛ ይሰጣል›› ቢልም በተጨባጭ እያየነው ያለው ብፁዓን አባቶች ከዚህ ዓለም በሞት በሚለዩበት ጊዜ ሀብት ንብረታቸው የወረሱትና እየወረሱት ያሉት የቅርብ ቤተሰቦቻቸው አባት፣ እናት፣ እኅትና ወንድም እንጂ ዕጓለ ማውታዎችና ችግረኞች አይደሉም።

የዚህ ዓይነቱ አካሄድ ደግሞ የቤተ ክርስቲያንዋን ጥንተ መሠረት የሚያናጋ ከመሆኑም በላይ ብፁዓን አባቶች በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ የነበራቸውን ተአማኒነት የሚሸረሽር፣ ንጽሕናቸውንና ቅድስናቸውን ጥያቄ ውስጥ የሚጨምር ነው።

‹‹ይረዷቸው ለነበሩ ዕጓለማውታና ችግረኞች›› የሚለው ሐረግም ቢሆን ተቀባይነት የለውም። በእርግጥ ምእመናንን በማስተባበርም ሆነ ቤተ ክርስቲያን ከምትሰጣቸው ደመወዝ ቀንሰው ረዲና ደጋፊ የሌላቸውን ሕፃናትና አረጋውያን የሚረዱ ብፁዓን አባቶች እንዳሉ እሙን ነው። በተግባር እንደምናየው ግን እነዚህ አባቶች ገና ከመጀመሪያው ያላቸው ገንዘብ ለዚህ መሰል በጎ ተግባር ስለሚያውሉት ከዚህ ዓለም በሚለዩበት ጊዜ የሚወረስ ቋሚ ንብረትና ቤት አልያም በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በባንክ ቤት አያስቀምጡም።

በትክክል እንኳን የእነዚህን ሊቃነ ጳጳሳት ‹‹የውርስ ገንዘብ›› ለሚያሳድጉዋቸው ዕጓለ ማውታ የሚውል ነው ቢባል ቤተ ክርስቲያንዋ የራሷ የሆኑ በርካታ የዕጓለማውታ ማሳደጊያ ማዕከላት ስላልዋት ሕፃናቱን ወደ ሚቀርባቸው ማዕከል በማዛወር የሊቀ ጳጳሱ ገንዘብና ንብረት

በሕገዊ አሠራር እነዚህን ማሳደጊያ ማዕከላት ወደሚያስተዳድረው ተቋም ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

እንዲህ ዓይነት ምቹ አማራጮች ባሉበት፣ ቤተ ክርስቲያንዋ በየዕንለ ማውታ ማዕከላት እያሳደገቻቸው ላሉት ሕፃናት ከውጭ ሀገር ሰዎች በሚገኝ የልመና ገንዘብ እያሳደገች በምትገኝበት ሰዓት በራሳቸው ጥረትና ልፋት ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመሆናቸው ብቻ ከምእመናን ያገኙትን ንብረትና ገንዘብ ‹‹ለዕንለ ማውታና ችግረኞች ማሳደጊያ›› በሚል ሽፋን የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ለሥጋ ዘመድና ለእኅት ልጅ ማውረስ ‹‹ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ›› ካልሆነ በስተቀር የብዕልና ተግባር ነው ለማለት ይከብዳል፡፡

እንዲያውም እውነቱን እንነጋገር ከተባለ የዘሬ ሊቃነ ጳጳሳት ከትና ንቶቹ በእጅጉ በተሻለ ሁኔታ ይኖራሉ፤ ከቤተ ክርስቲያንዋ አቅም ጋር ሲነጻጸር በቂ የሚባል ወርሐዊ ደመወዝ አላቸው፡፡ ሌላም ሳክል፣ ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን በገቢ በኩል በሁለት እግሮቿ ቆማ በመሄድ ያለችው የትናንቶቹ ብፁዓን ምእመናን ከልጆቻቸው በፊት ቤተ ክርስቲያናቸውን አስቀድመው ለቤተ ክርስቲያን አውርሰዋቸው ከሄዱ ሕንጻዎች ከሚገኘው ኪራይ አይደለም ወይ? የአሁኖቹ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላትስ እያማረጡ የሚለብሱት፣ እያማረጡ መኪና የሚዝኩት፣ በአውሮጳ ደረጃ በተሠራ ሕንጻ የሚኖሩት እነዚህ ብሩካን ምእመናን ትተውት በሄዱት ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት አይደለም ወይ?

ምነው ታድያ ‹‹ስለቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ሀብትና ንብረት›› የሚል ዓለማዊ ዓዋጅ ሲያወጡ ቢያንስ ‹‹ቅዱስ›› የሚለውን ማዕርግ አል ተውት? ቅዱስ የግል የሆነ ሀብትና ንብረት የለውምና፡፡ ከዚህ ሕግስ ምእመናን በአርአያነት የሚወስዱት ምን ይሆን? ለክብራቸው ሲባል በጠቅላይ ቤተ ክህነት ግቢ (ቅጽረ ቤተ ክርስቲያን) ዘመናዊ ቤት ተሠርቶላቸዋል፡፡ ሲታመሙ ቤተ ክርስቲያናችን ውጭ ሀገር ጭምር



እየላከች ተሳክማቸዋለች፡፡ ከዚህ ዓለም በሚለዩበት ጊዜ ለቀብርና ለጸሎተ ፍትሐት የሚያስፈልጉ ወጪዎች ሁሉ የሚሸፈነው በቤተ ክርስ ቲያን ነው፡፡ ሁሉም ሊቃነ ጳጳሳት አዲስ አበባ ሲመጡ (ከመደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ ወቅቶች በተጨማሪ) በየቀኑ ነጻ የምግብ አገል ግሎት አላቸው፡፡

በጠቅላይ ቤተ ክህነት ግቢ ውስጥ ለሁሉም ሊቃነ ጳጳሳት መኖሪያ ቤት መሠራቱ ሁሉም በጋራ በኅብረት መመገባቸው መልካምና ተገቢ አካሄድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሊቃነ ጳጳሳቱ ደመወዝተኛ ሆነው እያለ ከየአህጉረ ስብከታቸው ወደ አዲስ አበባ በመጡ ቊጥርና እዚሁ አዲስ አበባ ለሚኖሩ ጭምር ለምግባቸው የሚሆን ወጪ የሚሸፈነው ከቤተ ክርስቲያንዋ ግምጃ ቤት እየወጣ ነው፡፡

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ያሉ ሊቃውንት መምህራን የዕለት ጉርስ፣ የዓመት ልብስ አጥተው በሚቸገሩበት፣ ደቀ መዛሙርቶቻቸው ቀለብ አጥተው እየተበተኑ ባሉበት፣ ገዳማትና የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ለማስቀደሻ የሚሆን ጧፍና ዕጣን አጥተው እየተዘጉ በሚገኙበት፣ በአቅም ማነስ በሚል ምክንያት ስብከተ ወንጌሉ እየቀዘቀዘ በመጣበት ሰዓት፣ በመንፈሳዊ ኮሌጆች የሚማሩ ደቀመዛሙርት የተመጣጠነ ምግብና ልብስ ባላገኙበት ሁኔታ ሊቃነ ጳጳሳቱ ‹‹ምርጥ ምርጡን›› ለራሳቸው ማድረጋቸው የጤና አካሄድ ነው ብሎ ለማመን ይቸግራል፡፡

አባቶች ያቆዩን ሥርዓትና ባህል እናት ለልጆችዋ እንደምትራራ ሁሉ ብፁዓን አባቶችም ከራሳቸው በፊት ቤተ ክርስቲያናቸውን፣ ደቀ መዛሙርቶቻቸውንና ምእመናኖቻቸውን ነበር የሚያስቀድሙት፡፡ ያላቸ ውን፣ ያገኙትን ለቤተ ክርስቲያን ይሰጡ ነበር እንጂ የቤተ ክርስ ቲያን የሆነውን ‹‹የእርም ገንዘብ›› ለራሳቸው አያደርጉም ነበር፡፡ የትናን ትናዎቹ አባቶች ለራሳቸው ጥሬ ቆርጥመው ለእንግዳቸው የላመ የጣመውን የሚያጉርሱ፣ ለራሳቸው ከውስጥ ገላን የሚቆረቍር ማቅ ለብሰው የመንፈስ ልጆቻቸውን ለስላሳ ልብስ የሚያለብሱ ነበሩ፡፡

ነገሩ ተጠቃሎና ተጨምሮ ሲታይ አንቀጽ 45 ክርእሱ ጀምሮ ከመንፈሳዊነት ይልቅ ዓለማዊነትን የሚያንጸባርቅ፣ ግለኝነትን የሚሰብክ፣ የምንኩስናን ዓላማ የሚቃረን ነው። በዘመናችን ከዚህና መሰል ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ዙርያ በርካታ መጻሕፍትን ከጻፉት አንዱ አባ ገብረ መድኅን ከበደ ናቸው። አባ ገብረ መድኅን አሁን ያለው የቅዱስ ሲኖዶስ አካሄድን አስመልክተው በመጽሐፎቻቸው ካሰፈሩዋቸው መካከል ለአብነት ያህል ጥቂቶችን እንይ።

‹‹የቤተ ክርስቲያን ዓላማ የሥልጣን ጉጉት በሌለበት በሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ወንጌልን ማስተማር ነው። ቤተ ክርስቲያን ዓለማዊ ሽመትን፣ ሽልማትን፣ ራስ ወዳ ድነትን፣ ግለኝነትንና ዘረኝነትን ሳታስወግድ በክርስቶስ ስም እግዚአብሔርን ማገልገል አትችልም››[18]

‹‹የቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚጠነክረው የቤተ ክርስቲያን ቀመተ ሥጋ በመን ፈሳዊ ሕይወት እንደሚጠበቅ በሥጋዊ ሕይወትም ሲጠበቅ ነው። ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው እንደሚኖሩ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሀብተ ሥጋ ሁሉ በሥርዓተ ማኅበር ሥር ሲውል ነው፤ ከሠራተኛው አሠሪ ባለቤት ይበልጣልና ምንደኛው የደመወዝ ሠራተኛ ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ታማኝ ጠቢብ ቢሆን የሚችለው ያለምንም ደመወዝ በባለቤትነት የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ማኅበር የሚመሩ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት አባቶች ሲና ሩላት ነው።››[19]

‹‹የቤተ ክርስቲያን አባቶች የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ከሠርክ ጉባኤት፣ ከተሚላ መና ሪያ ቤትና ከተሚላ የክብር ልብስ በላይ ሌላ አያስፈልጋቸውም፤ ከደመወዝ ሞያተኛ ከምንደኛው ሠራተኛ ጋር ደመወዝ ከተቀበሉና የግል ቤት ከሠሩ ቤተ ክርስቲያን ባለቤት የላትም ማለት ነው።››[20]

‹‹መቼም ቢሆን እንደ ሊቀ ጳጳስ በር ዘግቶ ብቻውን አይበላም፤ ሰፊ የሆነ ማዕድ አለው፤ ይሁን እንጂ በደመወዝና በነፃ ሁለት ምግብ አንድነት እያሉ መብላት ከሥርዓተ ማኅበር አስተዳደር ውጭ ነው። እንዲ የዓመፃ ገንዘብ ስለሆነ ወደ ማኅበራዊ ሥርዓት ካዝና መግባት አለበት›› (ሉቃ.16:11)[21]።

[18] አባ ገብረ መድኅን ከበደ፡- የቤተ ክርስቲያን መጋቢ 2ኛ መጽሐፍ 1995 ገጽ.26

[19] አባ ገብረ መድኅን ከበደ፡- ሠርክ ጉባኤት 1998 ዓ.ም ገጽ.22

[20] አባ ገብረ መድኅን ከበደ፡- ሠርክ ጉባኤት 1998 ዓ.ም ገጽ.11

[21] አባ ገብረ መድኅን ከበደ፡- መቶ አጥፍ ዋጋ 2001 ዓ.ም ገጽ.19



# የማንታወቅ ይመስለን እንጂ ብዙዎች ያውቁናል

## 12ቁር. 6፥9፣ ቅዱስ ያሬድ

ጽጽስና መንፈሳዊ ክብርን የሚያጐናጽፍ ከፍተኛ መንፈሳዊ ማዕርግ ቢሆንም አስተዋይነትን፣ ብልኀነትን፣ ቅንነትን፣ ቅድስናንና ንጽሕናን አጣምሮ መያዝን የሚጠይቅና ከሥልጣን ይልቅ ለእግዚ አብሔር ታዛዥና ተገዥ ሆኖ በመገኘት ክብዙ ውጣ ውረድና ፈተና በኋላ የሚገኝ ከባድ ኃላፊነት ነው።

ብልኀና አርቆ አስተዋይ የሆኑ ሰዎች ለሹመትና ለሥልጣን የማይሽ ቀዳደሙትም ለዚሁ ነው። በዚህ በኩል ቤተ ክርስቲያናችን አኩሪ ተሞክሮ አላት። ይህ አኩሪ ታሪክ ከሐዋርያት የተወረሰ ባህል ነው። ሐዋርያት ተተኪዎቻቸውን የሚመርጡበት ራሱን የቻለ መንፈሳዊ ሥርዓት ነበራቸው። ይህ የሐዋርያት ሥርዓት በዓለም ላይ ከሚታየው ‹‹የዲሞክራሲያዊ አሠራር›› በእጅጉ የተሻለ ነበር።

ለምሳሌ ያህል አንድ ሁለት ማስረጃዎችን እንይ። በሐዋርያት ዘመን ስብከተ ወንጌሉ እየተስፋፋ መጥቶ የክርስቲያኖች ቍጥር እየበዛ በመጣበት ጊዜ መንፈሳዊ ተልእኮውን በሚገባ ማከናወን ይቻል ዘንድ ከአበው ሐዋርያት ጋር በመሆን የሚያገለግሉ ተጨማሪ ዲያቆናት (ደቀ መዛሙርት) መሾም እንዳለባቸው ታመነበት። በወቅቱ ሐዋርያት ራሳ ቸው ‹‹እገሌ፣ ብለው መምረጥ ይችሉ ነበር፣ ነገር ግን አሠራሩ ፍትሐዊ እንዲሆንና ከሁሉም በላይ ሕዝቡ ያመነባቸውን ለማስመረጥ በመፈለግ ተከታዮቻቸውን፡-

‹‹ከእናንተ ወገን በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላ ባቸውን ሰባት ሰዎች ምረጡ ለዚህ ሥራም እንሾማቸዋለን›› (ሐዋ. 6፥3)።

[1] በ2004 ዓ.ም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ እሾህ የሚለውን ዶግ ይለዋል። ዶግን ከሌላ እንጨት ሲያፋትጉት በቀላሉ እሳት ስለሚወጣው ዶግ ያለበት ጫካ ለእሳት ሰደድ በቀላሉ ይጋለጣል። በዛው ላይ ዶግ ከዛፎች ሁሉ ያነሰ ዕፅ መሆኑ ይታወቃል።

ባሉዋቸው መሠረት እስጢፋኖስን ጨምሮ ሰባት ዲያቆናት ተመርጠው ተሾሙ፡፡

ሐዋርያት ከቀጥታ ምርጫ ሌላ የአመራረጥ ዘዴም ይጠቀሙ ነበር፡፡ ይህም በጸሎት የሚከናወን ሥርዓት ነበር፡፡ ለምሳሌ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል ይሁዳ በገዛ ክፋ ሥራው ጌታውን በመሸጡና በመጥፎ አሟሟት ከሞተ በኋላ ሐዋርያት ተሰባስበው በምትኩ ሌላ ሐዋርያ ሊተኩ ፈለጉ፡፡ በእነርሱ እምነት ይሁዳን ሊተኩ ይችላሉ ወይም ደግሞ ከባዱን የሐዋርያነት ቀንበር ሊሸከሙ ይችላሉ ያሉዋቸውን ሁለት ደቀ መዛሙርት (ዮሴፍንና ማትያስ) ነበሩ፡፡ ይሁንና ከሁለቱ መካከል አገሌ ብለን ከምንመርጥ የሁሉን ልብ የሚያውቅ መንፈስ ቅዱስ በመሆኑ ሁኔታውን ይገልጽልን ዘንድ ሱባኤ እንግባ ብለው የጋራ ጸሎት ጀመሩ፡፡

በመጨረሻም እግዚአብሔር በገለጠላቸው አሠራር መሠረት በሁለቱም ላይ ዕጣ አጣጣሉ፡፡ በወጣው ዕጣ መሠረትም ማትያስ ዐሥራ ሁለቱኛ ሐዋርያ ሆኖ ተመረጠ (ሐዋ. 1፥22-26)፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው አበው ኢትዮጵያውያንም ከመካከላቸው አበምኔት አልያም እጲስ ቆጶስ ለመምረጥ ሲፈልጉ ከላይ የተጠቀሱትን የምርጫ ዘዴዎች ነበር የሚጠቀሙት፡፡

ለሹመት የሚታጨው አባትም ቢሆን ለምርጫ (ለውድድር) ከመቅረቡ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ በሚያዘውና አበው በደነገጉት ሕግ መሠረት፡-

- ጭምት
- ቃሉ የማይለወጥ
- የወይን ጠጅ መጠጣት የማያበዛ
- ከንቱ ትርፍ የማይወድ
- የሃይማኖት ምሥጢር የሚጠብቅ
- የማይከራ



- የማይቆጣ
- የማይጨቃጨቅ
- እንግዳ የሚቀበል
- ጻድቅና ቅዱስ የሆነ
- ራሱ ተምሮ ሌላውን ማስተማር የሚችል

የመሳሰሉትን መስፈርቶችን ያሟላ መሆን ነበረበት (1ጢሞ. 3፥7-8፤ ቲቶ. 1፥7-9)፡፡

ለኃላፊነት የታጨው አባት በበኩሉ «ትሾማለህ» ሲባል «እኔ ለዚህ ኃላፊነት ብቁ አይደለሁም» ሲል በትሕትና ይመልሳል፡፡ ይሁን እንጂ አባቶች በጋራ ሱባኤ ይዘው እግዚአብሔር ሲገልጽላቸው ወይም ደግሞ በጋራ ሆነው በሚጸልዩበት፤ በሚሰበሰቡበት ሰዓት እርግብ መጥታ ከታጩት መካከል በአንዱ ላይ ካረፈች ሹመቱ ከእግዚአብሔር የመጣ ጥሪ መሆኑ ስለሚታወቅ የተመረጠው አባት ኃላፊነቱን በትጋት ለመወጣት ቃለ ገብቶ ሥራውን ይጀምራል፡፡

ዛሬ ግን የጥንቱ የአበው ሥርዓት ተረስቶ (ሆን ተብሎ ተዘሎ) የአበው ምርጫ ዓለማዊ ቅርጽና ይዘት እየያዘ መጥቷል፡፡ «ምንኩስና በኢትዮጵያ» በሚለው መጽሐፌ እንዳሰፈርኩት ውስጥ ውስጡን ብቻ ሳይሆን በግላጭ «እኔን ምረጡ፤ እኔ እንድመረጥ እርዱኝ፤ አግዙኝ» እያሉ ግልጽና ስውር ዘመቻ የሚያካሂዱ «መነኮሳት» በተደጋጋሚ እያየን እያስተዋልንና እየታዘብን ነው፡፡ ትሾማለህ ሲባሉም ዛፎች ተሰብስበው እሾህን «መጥተሽ በላያችን ንገሺ» ሲልዋት «በእውነት እኔን በእናንተ ላይ ካነገሣችሁኝ እሳት ከእሾህ ወጥቶ የሊባኖስን ዝግባ ካልበላው ከጥላዬ በታች ታርፉ ዘንድ ኑ» እንዳለች ሁሉ ውስጣቸውን ሳይፈትሹ ለሥልጣን በመጓጓት ብቻ በፍጥነት እንደ እሾህ እሺ የሚሉ፤ ከተሾሙ በኋላም የደስ ደስ ድግስ የሚደግሱ ሆነዋል (መሳ. 9፥8-15)፡፡

በተቃራኒው ቤተ ክርስቲያናችን ዛሬም የጥንቱን የአበው መንገድ ተከትለው ወይንነታቸውን ሳያስደፍሩ፣ በወይራነታቸው እንደከሩ፣ የበለስ ጣፋጭነታቸውን እንዳስከበሩ የሚገኙ አባቶች አሏት። ይሁን እንጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ የዶጎቹ (አሾሆች) ቊጥር እየበዛ ብመምጣቱ አሁን አሁን እያየነው እንዳለ ከዶግ የሚወጣ እሳት ዝግባዎችን ማቃጠል ጀምሯል፤ የምናምንቴዎች፣ የዶግ (የእሾህ) ዘመን ደርሷል እንበል ይሆን?

‹‹እሾህ በወጋኝ ጊዜ ወደ ጉስቅልና ተመለስኩ›› (መዝ. 31፥4)።

‹‹ሕዝብም በእርሻ ውስጥ ተቈርጦ እንደተጣለና በእሳት እንደተቃጠለ እሾህ የተቃጠለ ይሆናሉ›› (ኢሳ. 33፥12)።

## ‹‹የውጪሲው እንቀጽ››

በ1991 ዓ.ም ከወጡት አዳዲስ የሕግ አንቀጾች መካከል ስለኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ በሚያወሳው በአንቀጽ 18 ቊጥር 3-ለ የሰፈረው እንዲህ ይነበባል፦

‹‹በዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፥ ባይሆንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ ሆኖ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቆ ያወቀ...››

በእንጻሩ ከ1991 ዓ.ም በፊት በየጊዜው በወጡ ደንቦች አንድ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ የሚሾም አባት ማሟላት ካለበት መስፈርቶች አንዱ ‹‹በዜግነት ኢትዮጵያዊ የሆነ›› የሚል አስገዳጅ ነጥብ ያካተቱ ነበሩ። በ1991 ዓ.ም ደንብ መሠረት አንድ ኤጲስ ቆጶስ የፈለገው አገር ዜጋ ይሁን የቤተ ክርስቲያናችን እምነት ተከታይ እስከሆነ ድረስ በኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ የመሾም፣ ቤተ ክርስቲያንዋን የመምራት መብት አለው ማለት ነው።



ይህ ደግሞ በአንድ በኩል ቤተ ክርስቲያንዋ የራሷ የሆነና ለአባትነት ብቁ የሆኑ ሰዎች የሉዋትም የሚል ትርጒም ከመያዙም በላይ ቤተ ክርስቲያንዋ ከግብፅ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ሥር ነፃ ወጥታ ራስዋን መምራት የጀመረችውን ጉዞ በመቀልበስ ዳግም ‹‹በባዕድ ቅኝ ግዛት ሥር›› እንድትወድቅ በር የሚከፍት አደገኛ አካሄድ ነው። ይህ ሕግ የወጣው የአሜሪካ ዜግነት ያላቸው ጥቂት አባቶችን ለማስተናገድ ተብሎ እንደሆነ መገመት ቀላል ነው።

በመሠረቱ እነዚህ ጥቂት አባቶች የፈለጉት ሀገር ዜግነት መያዝ መብታቸው ነው፤ የአገራችን ሕገ መንግሥት ይህንን ይፈቅዳልና። ይሁንና የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ጥምር ዜግነትን ስማይፈቅድ የሌላ ሀገር ዜጋ የሆነ ሰው በተደራቢነት የኢትዮጵያዊነት ዜግነት አይኖረውም። በሌላ አባባል የውጭ ዜግነት የያዘ ሰው ኢትዮጵያዊነቱን በፈቃዱ የተወ ማለት ነው።

በሌላ በኩል የውጭ ዜግነት ያላቸው ጳጳሳት ድንገት ጥፋት አጥፍተው ቢገኙ በኢትዮጵያ ሕግ መዳኘትም ሆነ መዳኘት አይችሉም ማለት ነው። በአንጻሩ ሥልጣን ላይ እስካሉ ድረስ አንዱን ጠቅመው ሌላውን መጉዳት፣ ብሎም በቤተ ክርስቲያን ሀብትና ቅርስ ላይ ጥፋት ሊያደርሱ ይችላሉ። ሰውን ቢጎዱ የራሳቸው ዜጋ፣ ቅርስ ቢዘርፉ የራሳቸው ሀብት አይደለምና። ስለዚህ ይህ ዜግነትን በተመ ለከተ የወጣው አንቀጽ እንደው ጫሲው 17ኛ አንቀጽ ውስጡ «መርዝ» ያዘለ በመሆኑ ባስቸኳይ ሊታረም ይገባል። በተለይ የውጭ ዜጋ ለሆኑ እንደ ካሪቢያንና ደቡብ አፍሪቃውያን ለመሳሰሉ የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ተብሎ የተቀረጸ ሕግ ከሆነም በግልጽ ሊሰፍር ይገባል።

## ብፁዓን ናችሁ

ባሮክ ኢየሩሳሌም በከለዳውያን ሠራዊት ከፈራረሰች በኋላ እንዲህ አለ፦

‹‹የዚችንም ከተማ ጥፋት አላዩምና አባቶቻችን አብርሃምና ይስሐቅ ያዕቆብም ብፁዓን ናቸው›› (ተ.ባ.2:27)።

እኔም ከዚህ ተነሥቼ እንዲህ ብልስ?

- ዳገት ቍልቍለቱን ተገዣችሁ፣ ፀሐይና ቊር ችላችሁ፣ እንደ አበው ሐዋርያት ደመና ጠቅሳችሁ፣ ክርስቶስን በኢትዮጵያውያን ልብ ዘርታችሁ፣ የኢትዮጵያ ጋራና ሸንተረሮችን በገዳማት አስጊ ጣችሁ ለደቀ መዛሙርቶቻችሁ ያስረከባችሁ፣ በወርቅና ዕንቍ አስጊጣችሁ የሠራችሁት ባለ ዐሥራ ሁለት መቅደስ የአኵስም ጽዮን ማርያም ቤተ ክርስቲያን በዮዲት ተቃጥሎ ሲፈርስ ያላያችሁ አብርሃና አጽበሃ ብፁዓን ናችሁ፡፡
- በእግዚአብሔር ፈቃድ ከመላእክት የዘማሬ ማዕድ ቀድተህ ያመጣኸውን ዜማ በስምህ ‹ዘመርን› እያሉ ዜማህን ከዘፈን ጋር እየቀላቀሉ በገንዘብ ሲቸረችሩት፣ ቃለ እግዚአብሔር እንደ ሐም ሌና ነሐሴ ዝናብ ሲፈስበት የነበረው መራደ ቃል ዐውደ ምሕረት የዳንኪራ መድረክ ሲሆን ያላየህ ቅዱስ ያሬድ ብፁዕ ነህ፡፡
- የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ስም ጠርታችሁ ሙታን ያስነሣችሁበትን፣ ጕርፍ የሞላ ወንዝ ከሁለት የከፈላች ሁበትን፣ አጋንንትን እንደጢስ ያበነናችሁበትን፣ ዘንዶን እንደ አክርማ የሰነጠቃችሁበትን መስቀል ለጮማና ቊርጥ፣ ለዊስኪና ኮርቫይዞር መባረኪያ ሲውል ያላያችሁ ኢትዮጵያውያን ጻድቃንና ሰማዕታት ብፁዓን ናችሁ፡፡
- ‹‹መነኮሴ ከመስቀል ማስቀመጫ በስተቀር ኪስ የለውም›› የሚለ ውን የአበው ሥርዓት አክብራችሁ፣ ከዓለማዊ ምግብ ይልቅ መን ፈሳዊ ስንቅን አስቀድማችሁ፣ የዓለም ነዳያን የሰማያዊ መን ግሥት ባለጸጋዎች ሆናችሁ፣ ሃይማኖታችሁን በደማችሁ ጭምር በማተም ለትውልድ አስረከባችሁ ያለፋችሁ፣ ዛሬ ስማችሁን ወርሰው፣ ልብሳችሁን ለብሰው፣ ከኪሳቸውና ሻንጣቸው አልፈው የገንዘብ ካዝና ተንተርሰው የሚተኙ፣ በቀን ሰባት ጊዜ ጸሎት



የሚለውን በቀን ሰባት ጊዜ መመገብ ወደሚለው ቀይረው ዓለ ማቸውን የሚቀጩ፣ በየከተማው የሚልከሰከሱ ‹‹ጥቋቁር ቍራ ዎችን›› ያላያችሁ አበው መነኮሳት ብፁዓን ናችሁ፡፡
- ከኪራዩ በሚገኘው ገንዘብ ዕጓለ ማውታ አሳድጉበት፣ ለገዳማት የሚውል ዕጣን ዘቢብና ጧፍ ግዙበት፣ የታረዙትን አልብሱበት፣ የተራቡትን አጥግቡበት፣ የአብነት መምህራንና ደቀ መዛሙር ቶቻቸውን እርዱበት ብላችሁ የግል ቤታችሁን ለልጆቻችሁ ሳይሆን ለገዳማትና አድባራት አውርሳችሁ ያለፋችሁ ምእመናን፣ ከቤቶቻችሁ የሚገኘው የኪራይ ገንዘብ ለግል ቤት መሥሪያ፣ ለዘመድ አዝማድ ማቋቋሚያ፣ ‹‹ለሽርሽር መኪና›› መግዣ ወዘተ ሲውል ባለማየታችሁ ብፁዓን ናችሁ፡፡

## ሙስና ነክ ቅኔዎች

በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ሙስና የነበረና ያለ ቢሆንም ጥንትም ሆነ ዛሬ ይህንን የሙስና አሠራር የሚቃወሙ በርካታ ሊቃውንት አባቶች ነበሩ፤ ዛሬም አሉ፡፡ ሙስናን ለመቃወም ከሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች (መሣሪያዎች) አንዱ ደግሞ ቅኔ ነው፡፡ በዚህ መስክ የተደረሱና የተነገሩ ቅኔዎች እጅግ ብዙ ቢሆኑም ለአሁኑ አንድ ሦስቱን ‹‹እንደ ማስረጃ›› ላቅርብ፡፡

### ዘአድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)

(ሥላሴ)

ኢትክሉ ተቀንዮተ
ለእግዚአብሔር ወለንዋይ
ለዘይብለከ አምላክ ሰማዒ መቅድመ ኵሉ ታፍቅሮ
ለገብርከ አፍቅሮ ንዋይ ይእዜ ሰዐሮ፣

እመሰ ለወርቅ አፍቀርኮ ወአስተባዛኅኮ ክብሮ
እንዘ በጥንቁቅ ታነብሮ
አእምር አእምር አእምሮ
ከመ ኮንከ ለንዋይ ገብሮ።

## ትርጉም

‹‹ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ
መገዛት አትችሉም›› ያለህን
አምላክ ሰሚ! ከሁሉ በፊት ታፈቅረው ዘንድ
አገልጋይህ (ገንዘብ) መውደድን ዛሬ አለናብተው፣
ወርቅን ብትወድ ክብሩንም ብታበዛ
በጥንቃቄ እያኖርኸው
የገንዘብ አገልጋይ እንደሆንህ
ማወቅን እወቅ፣ እወቅ።

## ምስጢር

**‹‹አንድ አገልጋይ ለሁለት ጌቶች መገዛት አይቻለውም›› እንደ ተባለ እግዚአብሔርን እወዳለሁ የሚል ሰው ገንዘብን በጣም የሚያፈቅር ከሆነ የእግዚአብሔር ወዳጅ ሊሆን አይችልም በማለት ለገንዘቡ ሲንሰፈሰፍ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም የሚያዳግተው መሆኑን ባለቅኔው ያስገነዝባሉ።**[1]

[1] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር፦ የግእዝ ቅኔያት የሥነ ጥበብ ቅርስ 2ኛ ክፍል ንባቡ ከነትርጓሜው (ገጽ 223-244) 1984 ዓ.ም።



## በቁስ ገበና (ሽሽቃ)

(መወድስ)

እምኮኖ ጌጋየ በመዋዕሊነ
ለዳዊት ንጉሥ ቃለ ብሂሎቱ ፍሉጥ
ይለብሱ ጽድቀ ካህናተ አፍኣ ወውስጥ፣
እንዘ እምነቶሙ በመክፈልት ኅዳጥ
እስመ ብኩርናሆሙ ያመስጥ
ወታቦተ ሕግ ልቦሙ በወርቀ ዕበድ ልቡጥ።
ቀሲስ ኢይከውን ወርቀ ዐመፃሆሙ ሂጥ
በእደ ቢጹ ወኢያሶን ኅሰፍተ እከይ ይትመያየጥ
እንዘ መድሎቱ ሐሰት በዐውደ ይሁዳ ተውሳጥ
አምጣነ ንባቡ በቃለ ጽርዕ ወትርጓሜሁ በዕብራይስጥ።

## ምስጢር

የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት በመዝሙሩ ‹‹ካህናት ጽድቅን ይለብሳሉ›› ብሎ እንደዘመረላቸው እንደ እውነተኞች ካህናት ያይደሉ ካህናት እምነታቸው በመብልና በመጠጥ፣ በሹመትና በገንዘብ ስለሆነ ዳዊት ይህን በመዝሙር የዘመረው በዘመናቸው ለነበሩ ካህናት ቢሆን ያስነቅፈው ነበር ይላሉ ባለቅኔው። ወርቅ ክብረትና ክብር የሳቀ ዋጋ እንዳለው የአዋቂ አጥፊዎች የሆኑ ካህናትም በደል ቀላል አይደለም። በተሰሎንቄ በኢያሶን ቤት ውስጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስና ደቀ መዝሙሩ ሲላስ ወንጌልን እየሰበኩ ብዙ ሰዎችን አሳመኑ። አይሁድም ‹‹ኢየሱስ የሚባል ሌላ ንጉሥ አለን በማለት የቄሳርን ትእዛዝ ይቃወማሉ›› ብለው ጳውሎስን፣ ደቀ መዝሙሩንና አዲሶችንም ክርስቲያኖች ቢወነጅሏቸው ኢያሶንና ወንድሞቹ ዋሶች ሆነው እንዳስፈቷቸው የካህናቱም በደል በየዕለቱ የሚፈጸም ሆነ።

ሚዛን ዕቃን በገንዘብ ለመግዛት፣ ወይም ዕቃን ለመለወጥ መለኪያ በመሆን እንደሚያገለግል፣ የካህናቱም ዐመል በአደባባይ መምህሩ ኢየሱስን አሳልፎ ከሰጠ ከአይሁድ ተንኮል ጋር አንድነት አለው። የዐመፃቸውም መሠረቱ ስሙ በግሪክኛ ዲያብሎስ፣ በዕብራይስጥ ሰይጣን የሚባለው የጨለማ መልአክ ስለሆነ ከእውነት ይልቅ ሐሰት ይቀናቸዋል በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል (ሐዋ.17፡5-9)[2]።

## (ክፍለ ዮሐንስ-ዘጉንደር)

### (መወድስ)

እምከዊነ ካህን ይኄይስ ከዊነ ኖላዊ
ወኅለ እንስሳ ትትበደር እምቤተ መቅደስ ዐባይ
እስመ ቤተ መቅደስ ኮነት ቤተ ፈያታይ፤
ወበላዕለ ኖሎት ኢሀለወ
በላዕለ ካህናት ዘሀሎ እከይ፤
ተእምርተ ዝኒ ከመንርአይ
በኅለ እንስሳ ሠረቀ ዘኢየዐርብ ፀሐይ
ወኖሎት ተዛውዑ ምስለ ሐራ ልዑል ሰማይ።
ዓዲ እምቅድመ ዝንቱ እመካነ ኖሎት ወመራዕይ
ከመ ተጸውዑ ደምፀ እግረ ቃለ ዜና ሠናይ
ወልደ እንበረም ለምስፍና ወለቅብዐ መንግሥት ወልደ እሴይ።

### ትርጉም

ካህን ከመሆን እረኛ መሆን ይሻላል
የእንስሶች በረትም ከታላቅ ቤተ መቅደስ ትመረጣለች።

[2] በተራ ቍጥር 1 የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 375-376



ቤተ መቅደስ የሽፍታ ቤት ሆናለችና፤
በካህናት ላይ ያለ
ክፋትም በእረኞች ላይ የለምና፤
የዚህንም ምልክት እናይ ዘንድ
የማይጠልቅ (የማይጨልም) ፀሐይ በእንስሳ በረት ወጣ፣
እረኞችም ከከፍተኛ ሰማይ ጌታ መላእክት ጋር
አብረው ተጫወቱ።
ዳግመኛም ከዚህ በፊት ከእረኞችና ከመንጎች ቦታ
የእንበረም ልጅ (ሙሴ) ለመስፍንነት የእሴይም
ልጅ (ዳዊት) ለመንግሥት ቅባት እንደተጠሩ
የመልካም ወሬ ኮቴ ተሰማ።

### ምስጢር

«እናትና አባት ብዙ ይወልዳሉ፣ ሙያውንና ግብሩን አይተው አንዱን ይወዳሉ›› እንዲሉ መወደድና መላቅ ከሥራ መበጀት የተነሣ ነው። እረኞች ከብቶቻቸውን ከማሰማራትና እርስ በርስ ከመጫወት በቀር ሌላ ተንኮል አለማሰባቸውን ስጊዜው በጨዋታም ቢጣሉ ወዲያውኑ መስማማታቸውን ከቅንነታቸውም የተነሣ ክርስቶስ በእንስሳት በረት ሲወለድ እነርሱ ከመላእክት ጋር ማመስገናቸውን በማመልከት ባለቅኔው ከካህንነት እረኝነት፣ ከቤተ መቅደስ በረት ይሻላል ይላሉ።

ደግሞ ክርስቶስ ስለቤተ መቅደስ ሲናገር «ቤቴ የጸሎት ቤት ነበር፣ እናንተ ግን የቀማኞችና የሌቦች ቦታ አደረጋችሁት›› እንዳለ እውነት ሊነገርባትና ሊሠራባት የተመሠረተችው ቤተ መቅደስ ማታለያና መቀሰጫ ስትሆን የከብቶች በረት ግን የክርስቶስ መወለጃና የመላእክት ማመስገኛ መሆኗን ገልጠዋል።

ጥንቱንም ሙሴ ለመስፍንነት የእሴይ ልጅ ዳዊትም ለመንግሥት የተመረጡት ከበጎችና ከእረኞች መካከል እንጂ ከቤተ መቅደስና ከካህናት መካከል አለመሆኑን ጠቅሰው ታላቁ ሊቅ ክፍለ ዮሐንስ በዐሥራ ስባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን የካህናትና ማኅበራዊ ግንኙነት በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል።[3]

[3] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር፦ የግእዝ ቅኔያት የስነ ግጥም ትርስ ንባብና ትርጓሜው (የመጀመሪያ እትም) ፦1980 ገጽ 393-394



# ዋቢ መጻሕፍት

1. አባ ገብረመድኅን ከበደ፦ የቤተ ክርስቲያን መጋቢ 2ኛ መጽሐፍ 1995
2. አባ ገብረመድኅን ከበደ፦ ሥርከ ኅበስት 1988
3. አባ ገብረመድኅን ከበደ፦ መቶ እጥፍ ዋጋ 2001
4. ደስታ ተክለ ወልድ፦ ገበታዋሪያ የንባብ መማሪያ 1928
5. ዜና መዋዕል ዘብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ሐምሌ 5 ቀን 1989 ዓ.ም
6. ዝክረ አበው መጽሔት 1996 ዓ.ም
7. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ 1945 ዓ.ም ሕገ ቤተ ክርስቲያን (ያልታተመ)
8. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሕገ ደንብ 1971 ዓ.ም (ያልተተመ)
9. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሕገ ቤተ ክርስቲያን 1988 ዓ.ም (ያልታተመ)
10. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ሕገ ቤተ ክርስቲያን 1991 ዓ.ም (ያልታተመ)
11. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ታቦተ ጽዮን በኢትዮጵያ፦ ጥር 2001 ዓ.ም

12. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡- መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት 8ኛ እትም

13. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር፡- የግእዝ ቅኔያት የሥነ ጥበብ ቅርስ መጀመሪያ እትም ንባቡ ከነትር ጓሜው 1984

14. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር፡- የግእዝ ቅኔያት የሥነ ጥበብ ቅርስ 2ኛ ክፍል ንባቡ ከነትር ጓሜው 1986

15. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፡- መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ 1945 ዓ.ም

16. ፈለገ ጥበብ መጽሔት፡- ሚያዝያ - ሰኔ 1992

17. ፍስሐ ጽዮን ካሣ (መምህር) መርኆ 1983

18. DARLUS AT SUSA – Kahyn international (Sep. 14,1964)